አዘጋጅ
ዳምጤ አሰማኸኝ
EDITOR
DAMTE ASSEMAHEGN

ሞዓ አንበሳ

የመስከረም እትም P.O.Box 9056 ALEXANDRIA VA, 22304 TEL. (703) 998-5152 ዋጋ $1.5o

ርዕስ አንቀፅ

ቤተ ክርስቲያን የገባች ውሻ!!

የወያኔዎች ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ነሐሴ 10 ቀን 1994 ዋሽንግተን ዲ.ሲ ገባ። ከአሥር የማይበልጡ የወያኔ ቡችሎች ያችን የጠሏትን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተሸክመው ተጠባበቁት። አንድነቱን አጥብቆና ተሠልፎ የመለስ ዜናዊን ወደዚህች አገር መግባት ይቃወም የነበረው አሥርሺህ ሕዝብ ምቹ ጊዜ አጋጠመው።

መለስ ዜናዊ ይጓዝበት በነበረው አውቶሞቢል ላይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የለም። በግራና በቀኝ ሰዎች በእናቱ ቀሚስ ውስጥ እንደ ተሸሸገ አድርገው ሸፍነው ይዘውታል። በአንድነቱ የፀናው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የድንጋይ ናዳ በመኪናው ላይ ሲያወርድ ለጉድ ታየ። ኢትዮጵያውያን የሴት ወጣቶችም የገማ ዕንቁላልና ቲማቲም በግንባሩ ላይ አፈረጡ።

ከመለስ ዜናዊ መኪና ቀጥሎ የወያኔው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሥዩም መስፍንና የንሬዚዳንቱ የግል ሐኪም የያዘች አውቶሞቢል ታየች። ዮሴፍ ግዛቸውና ካሣሁን ተፈሪ የተባሉ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች መኪናዋን በግራና በቀኝ ከፍተው ተቃውሞአቸውን በተግባር አሳዩ።

ከዚያ ሁሉ አሥር ሺህ ኢትዮጵያዊ ጥቂቶቹ ያለ አግባብ ተይዘው ታሠሩ። መለስ ዜናዊም የመንግሥታት ተወካይ መሪዎች የሚያርፉበት ቤትና ሆቴል ተነፍጐ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ ተሸሽጐ መቀመጥ ግድ ሆነበት። ኤምባሲውም ለአንድ ሳምንት ዝግ መሆኑን አስታወቀ።

አክራሪው የኢህአፓ ኮሚዩኒስት መለስ ዜናዊ ከደርግ የተረከበውን የሕዝብ ርስትና ንብረት ይዞ በሀብቱ ይጠቀምበታል። የመለስ ዜናዊም የበላይ ኃላፊ ኢሣይያስ አፈወርቂ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እያሟጠጠ ኢትዮጵያ ራቁቷን እንድትቀር ይጥራል። ታላቁ የአሜሪካን መንግሥት የኢትዮጵያን ጥንታዊ ወዳጅነትና ባለ ታሪክነት ይዘነጋል ብለን አናምንም። ትናንት ኢትዮጵያን በኮሚኒስቶች እስከ ተወረረችበት ጊዜ ድረስ ርስትና ንብረቷን አስከብራ ሕዝቧን በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ለማስተዳደር ትጥር እንደ ነበረ ይታወሳል።

የወያኔው አክራሪ ኮሚዩኒስት ፕሬዚዳንት ለወገኖቹ ለአድዋ ሕዝብ የከተማ ቤትና ቦታ ለሕዝቡ እንዲመለስ ሲያደርግ፣ የጀግናውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ርስትና ንብረት ቀምቶ ለመኖር እንደማይችል እናረጋግጥለታለን። ንብረት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ አውታር መሆኑንም በቅርብ ቀን እናስተምረዋለን። በሕይወቱ ቆሞ ለማየት ስለማይችል ግን እናዝንለታለን። የአሜሪካን አገር ጉብኝቱም በጀግናው የኢትዮጵያ ወጣትና ሕዝብ ተወግዞ መድረሻ በማጣቱ "ቤተ ክርስቲያን የገባች ውሻ" አድርጐታል ይኸንንም የነፃነታችን ምልክት አድርገን እንመካበታለን።

የወያኔው ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊ "ከበደ" የሚባለው የኢህአፓ ባልደረባ እየጻፈ የሰጠውን የአሜሪካን አገር ጉብኙቱን ተቀባይነት እንዳገኘ አስመስሎ የፕሬዚዳንት ክሊንተንን አቀባበል ጭምር ተናግሯል። ይህ ሁሉ ሐሰት መሆኑንና በቻነል 5 በኢትዮጵያ ውስጥ ረኃብ የለም ያለው የሐሰት ቃል የባሰውን ሕዝቡን አስቆጥቶታል። ተሰጥቶት የነበረውም ፕሮግራም የተሠረዘ መሆኑን እናረጋግጣለን።

"CHASING A-DOG OUT OF THE CHURCH

On August 10th 1994 the "Woyane Ethnic President was in Washington D.C. He was welcomed by ten of his Ethnic Group supporters carrying the Ethiopian Flag, the flag once hated by the "Woyane" Ethnic group. Also in Washington D.C. on this date were ten thousand Ethiopian that opposed the "Woyane Ethnic President". The "Woyane Ethnic President was on his way to the State Department, usually the country's flag is displayed on the car. But on this date the Ethiopian flag was not present on the car. It was if the people around him were trying to shield him or protect run from being seen or killed by the United Ethiopians. He was eventually seen in his car by the United Ethiopians; it was if the "Woyane President" was hiding himself under his, mother's dress. The heroes of the United Ethiopians started throwing stones at the car; the women threw rotten eggs and tomatoes which hit the "Woyane President" in the face. In the car following the "Woyane President were his Foreign Minister "Seyoum Mesfin" and the "Woyane President's private Doctor who were pulled from their car and beaten by Yoseph Gizachew and Kassahun Tefera until help arrived. They were beaten by these Ethiopian heroes. After it was over, these Ethiopian heroes were arrested, and were released after two days. America is the land of freedom and democracy, unlike the country ruled today by the "Woyane President."

cont'd. on page. 2

የገጽ ማውጫ

ተራ ቁ. ርዕስ አንቀጽ
ቤተ ክርስቲያን የገባች ውሻ ሆነ (መለስ ዜናዊ) 1
Chasing a dog out of the church 1
አንበሳው አሥራት ወልደየስ 2
አጭር የሕይወት ታሪክ 3
(ስለ ፕሮፌሠር አሥራት) 3
ከሕግ ውጭ የተበተነው ጽሑፍ
የታሪክ እንቅፋት (ስለ ልዕልት ተናኘ) 3
ልዑል ራስ መንገሻና የትግራይ ድርጅቶች 3
ስለ ኢዲዩ ድርጅት 5
ሕግ ጠቀስ ደብዳቤ (አፈንጉሥ ተሾመ ኃ/ማ.) 5
እቴጌ መድፈሪያሽ ወርቅ ማናቸው? ከኃይሉ በለጠ 7
ስለ ልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ ለሞዓ አንበሳ ጋዜጣ አዘጋጅ የተላለፈ ውሳኔ 7
ሹመት 8
ማሳሰቢያ 8
አዲተር ሊያጣራው ነው 8
የጂቡቲው ደብዳቤ (ስለ ልዕልት ማርያም ሥና) ከሐምሌው እትም የቀጠለ 8
በደርግ ላይ የታደመውና በኛም ላይ የተፈጸመው (ኢሣይያስና መለስ) 9
ቢወልደኝ ንጉሥ (ስለ ደጃዝማች ከበደ ተሰማ) 9
የአንድነት ጥሪ 10
የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት 10
ዝግጁነታችን እርግጠኛ ነው 10
ታሪክን በደማቸው የገነቡ (ታሪካዊ ግጥም) 11
ከደርግና ከወያኔ ጋር የተደረጉ ጦርነቶች ከሐምሌው እትም የቀጠለ..... 11
ስለ ኢትዮጵያ "በኮንግሬስ የተካሔዱ ውይይቶች" 11
ኰሎኔል ሣሙኤል ይቅርታ ጠየቀ 12
የታሪክ እንቅፋት (ከሐምሌ እትም የቀጠለ) 12

continued from page 1

The E.P.R.D.F. "Woyane President, Mellese Zenawi" is a communist of the Ethiopian peoples Revolutionary party. The Derg, who is Mengistu's party and Mellese of E.P.R.P are both communist. Ethiopia is fed up living under the communist yoke. "Enough is enough."

"Mellese Zenawi was not treated well in Washington D.C.. He met President Clinton for 11 minutes only including many other African leaders. He stayed at the Ethiopian Embassy, which was closed to the public during his stay there.

The E.P.R.P. communist Melles Zenawi is doing the same thing the former communist president Mengistu Hailemariam did to the Ethiopian people, confiscating public property and using the money for himself and his party.

The commanding president over Melles Zenawi, is Isayiyas Afeworki of Eritrea, a long time communist who studied communism in China during "Mao Tsetung's rule. Isayiyas is trying to take every penny from EThiopia back to his country. This will stop when Melles no longer "Woyane President in Ethiopia.

Ethiopia was known as a free country throughout the world. Ethiopia has tasted the Capitalist Economy of "Adam Smith, and can never learn the bitter communist Economy of Karl Marx. This is why we hate Mengistu, and why we do not want to see Melles Zenwi, who is the worst and most hated human being in Ethiopia. How can you trust a communist who lied on National Television, that there is no starvation in Ethiopia.

Ethiopians are known to be a proud black race in Africa, and has never bowed down for the European colonialist in history.

When British Colonialist tried to invade Ethiopia Emperor Teodros took his pistol and shot and killed himself, because he couldn't see his country ruled by colonialist. When the British saw what this Great man did for his country, they left Ethiopia as they found it "Free." In 1888 Italy tried to invade Ethiopia Emperor Menelik of Ethiopia fought back with everything he had. And the Italian Colonialist could not conquer Ethiopia. Thousands were captured in those days.

Again in 1935 the Italian Fascist tried again to invade Ethiopia. "This is when our Back American brothers fought with us side by side and shed their blood along side Ethiopia." Our victory is theirs. That is what history is to Black people.

We the people of Ethiopia don't believe that this Great country of the United STate will forget Ethiopia who has been a long-time friend throughout history.

Read "Sons of Sheba's Race"
D.T. 387. 857 The chapter on African Americans & the Italian Ethiopian War.

In his native land the "Woyane Ethnic President has freed all the properties confiscated in Adwa. He is still holding all the properties and lands in Ethiopia.

Capitalist Economy was the main structure of Ethiopia. That is why we can not go along with the "Woyane Ethnic President."

The "Woyane Ethnic President has been using a communist party member called "Kebede" who prepares the president's speeches etc.

Kebede wrote how president Clinton welcomed the Woyane President and how President Clinton treated him like a hero. It's all a lie. The Ethiopian people here have never heard such a story from President Clinton as written by Kebede during "Mellese Zenawi's stay in Washington D.C.

As long as freedom exists for every person on earth the "Woyane President should know he can never rule Ethiopia. If we can not free ourselves from the communist yoke - then we will all die - " But our children will be free by our blood tomorrow."

እንበሳው እሥራት ወልደየስ

ለአምላክ ምሥጋና ይግባውና፣ የታሪክ ንግሥት ለሆነችው ኢትዮጵያ፣ የታሪክ ልጆች ነሥቷት አያውቅም። ከማሲንቆአችንም ባገኘነው ትምህርት "ሰው ማለት፣ ሰው ማለት፣ ሰው ማለት ሰው የሚሆን ነው፣ ሰው የጠፋ ዕለት" ሲል "ዘሾ" የተባለው ቀስታሽ አዝማሪ በታሪክ አስተምሮን አልፏል።

ሆኖም ባሁኑ ጊዜ አገራችን ሰው አጣች ማለታችን ሳይሆን፣ ከብዙዎች ቀድሞ፣ "እኔ አለሁላት" በማለት ለታሪክ ተሽቀዳድሞ የሚመዘገብ ሰው ማለታችን ነው። ይኸንንም ስንል፣ እንደ ኃይሉ ሻውል ያሉትን አይደለም። አንድ እሥራት ወልደየስ ቢታሠር፣ ኢትዮጵያ ብዙ ሚሊዮን እሥራት ወልደየሶች እንዳላት ጠላቶቻችን እንዲያውቁ እንፈልጋለን። ስለዚህም ኢትዮጵያ አገራችን መሐን አይደለችምና የብዙ ሚሊዮን ጀግኖች እናት የአምስት ሺህ ዘመናት የታሪክ ንግሥት መሆኗን ግጤን ያሻል። ጠላቶቻችን ከብዙ ዘመናት ጀምሮ የኢትዮጵያን አንድነት ለመፈታተን ከመጠን በላይ ሞክረዋል። ወገኖቻችን የምንለውን የትግሬና የኤርትራ ተወላጆች በመገንጠል፣ የእኛን አንድነት ለማለያየት በብዙ ጥረዋል። በባሕላችን፣ በሃይማኖታችን፣ በአለባበሳችን፣ በቋንቋችንና በፊደላችን የማንለያየውን ሕዝብ እንድንጣላ ሞክረዋል። ምሥጢሩ በያንዳንዱ የትግሬና የኤርትራ ተወላጆች ልብ ውስጥ ተቀብሮ እንደ እሳት ከመንደድ ላይ ይገኛል። መሪ ነን በማለት ሕዝቡን የሚያወናብዱትን የአሻንጉሊት ፕሬዚዳንት ኢሣይያስ አፈወርቂንና፣ የአሻንጉሊት ምክትል ፕሬዚዳንት መለስ ዜናዊን በጥርስ የሚገነጣጥሏቸው ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

ፕሮፌሠር እሥራት ወልደየስ ታሪክ ያቀረበው ጀግና ሲሆን፣ ኤርትራም ሆነች ትግሬ የኢትዮጵያን አንድነት ጠብቀው ለታሪክ ያስተላለፉ ጀግኖች ነበሩዋቸው። እንደ አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም እንደነ አሰፋ ባህታ ያሉ ሁሉ የኢትዮጵያ ታሪክ ችቦ ሆነው ለናት አገራችን ሲያበሩ ይኖራሉ። ፕሮፌሠር እሥራት ወልደየስም ከነዚያ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ጀግኖች ጋር ተሠልፎ ይገኛል። ከጀግኖች አባቶቹ የተረከበውን የአምስት ሺህ ዘመን የነፃነት ታሪክ ለተተኪው ትውልድ ለማስተላለፍ ወቅቱ ጠርቶት በሠልፉ ወስጥ ሥፍራውን ይዞ እስከ ሞት ፅዋ ያገሩን ነፃነት ይጠብቃል። ፋሺስትና ኮሚዩኒስት የሰውን ልጅ በመግደል የሚያምኑ ናቸው። የኢትዮጵያ ልጆች ግን ሞት የማይበግራቸውና "ማነህ ባለ ሳምንት" ብለው የሠልፉን ቅድሚያ ለመያዝ ሲሽቀዳደሙ ይገኛሉ።

ደም እንደ ጉርፍ ሲወርድባት የኖረች አገር የነፃነቷ ዋስትና ደም መሆኑን ታውቀዋለች። ከሰንደቅ ዓላማዋ ገርጌ በቀይ ቀለም የተዘጋው በልጆቿ ደም የኖረው የነፃነት ምልክት ነው። ኢትዮጵያን በቅኝ ለመግዛት ፋሺስቶች ሞክረው አቃታቸው። እንግሊዞችም አገራችንን በቅኝ ለመግዛት ሞክረው አባ ታጠቅ ካሣ (ቴዎድሮስ) ሽጉጣቸውን ጠጥተው በመሞት እንዲመለሱ አደረጓቸው። ወገንን ከወገን ለማለያየት፣ ለማጋጨት ሞክሮ የነበረው የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ኮሚዩኒስት ፓርቲና የወያኔው አክራሪ የኢህአፓ ኮሚዩኒስት ፓርቲ ሕዝቡን እርስ በርስ ለማጋጨት ሞክሮ ሲታወቅበት መግቢያ አጣ።

ኢትዮጵያን ከሆዳሞች መንጋጋ ለማላቀቅ ደም እንደ ጉርፍ መውረዱ ግልጽ ነው። ኢትዮጵያ በአንድነቷ ፀንታ የአምስት ሺህ ዘመን ታሪኳን ጨብጣ ትረመዳለች። ወደ ፊት ከመራመድ አታቋርጥም። ፕሮፌሠር እሥራት ወልደየስ ያገሪቱን ጥሪ አክብሮ በሠልፉ ውስጥ ተገኝቷል። የዘመኑ ታሪክ ባለቤት ሆኖ ተተኪውን ትውልድ ሥፍራ ለማስያዝ በቆራጥነቱ የዘመኑ ጀግና ተብሏል። ማነህ ባለሳምንት እያልን በብዙ ሚሊዮን የምንቆጠር ኢትዮጵያውያን የአንበሳውን የእሥራት ወልደየስን ሥፍራ ይዘን ደማችንን ለኢትዮጵያ አንድነት ለማፍሰስና ነፃነቷን ለመጠበቅ ተሠልፈን እንገኛለን። ተእንግዲህ ወዲህ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ እንደማይመለስ ወያኔዎች ይወቁት።

(እናንተ ትጠፉዋታላችሁ እንጂ፣ ኢትዮጵያ አትጠፋም።)

እሥራት ወልደየስ (ፕሮፌሠር)

አጭር የሕይወት ታሪክ

ፕሮፌሠር አሥራት ወልደየስ ሰኔ 12 ቀን 1920 ዓም ተወለዱ። ዕድሜያቸው ሦስት ዓመት ሲደርስ፣ ቤተ ሰቦቻቸው ወደ ድሬደዋ ተዛወሩ። በሰባት ዓመት እድሜያቸው የአማርኛ ንባብና ጽሕፈት ተማሩ። ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ፣ የፈረንሣይኛ ቋንቋ ለመማር ተዘጋጁ። ወላጅ አባታቸውን ፋሺስቶች ገደሏቸው። የቤተ ሰቦቻቸው ዓላማና የራሳቸውም የትምህርት ዕቅድ በዚህ ሁኔታ ሲደናቀፍ አያታቸው ቀኛዝማች ፅጌ ወረደ ወርቅ የጦር ዕሥረኛ ሆነው ከተወሰዱበት ከኢጣሊያን አገር ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ገቡ። ከዚህ በኋላ ወጣቱ ፕሮፌሠር አሥራት ከአያታቸው ጋር ወደ አዲስ አበባ ተዛወሩ።

እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በ1934 ዓም ፕሮፌሠር አሥራት መደበኛ ትምህርታቸውን በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ቀጠሉ። በትምህርት ክፍላቸው ውስጥ በአንደኛነት ስለ ወጡ፣ አሌግዛንድሪያ (ግብፅ) ወደሚገኘው ወደ "ቪክቶሪያ ኮሌጅ" ተላኩ። ከመጀመሪያው የትምህርት ክፍለ ዓመት በኋላ ለሚቀጥለው የትምህርት ዓመት በቂ ችሎታ ያላቸው ሆነው ተመረቁ። አምስት ዓመት ሊወስድባቸው ይችል የነበረውን የትምህርት ፈተና ጥሰው ወደ "ኤድንብራ ስኮትላንድ" የሕክምና ኮሌጅ ለመግባት ሁለት ዓመት ይፈጅ የነበረውንም አልፈው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ፈተናውን አለፉ። በዚህ ዓይነት ከኢትዮጵያውያን የሕክምና ተማሪዎች ዋና ሆነው ተገኙ። ወደ ውጭ አገር በዘመኑ ከተላኩትም ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ውስጥ ዓርባ ሁለተኛው ነበሩ። ፕሮፌሰር አሥራት በሕክምና ሞያ ከተመረቁ በኋላ ለአንድ ዓመት ያህል "በኤድንብራና" በኢትዮጵያ ውስጥ የሕክምና ጥናታቸውን በተግባር ላይ በማዋል ቆዩ። በ1956 የሕክምና ሞያቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው የልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል በማገልገል ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ሐኪም መሆናቸው ታወቀ። ከአምስት ዓመት የሕክምና አገልግሎታቸው በኋላ፣ የቀዶ ጥገና ትምህርታቸውን ለማላቅ "በስኮትላንድ" ወደሚገኘው የቀዶ ጥገና "ሮያል ኮሌጅ" እንግሊዝ አገር ተጓዙ።

ፕሮፌሠር አሥራት የኤርትራን መገንጠል እውግዘው በወያኔዎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እስከ ተባረሩ ድረስ በልዕልት ፀሐይ ሆስፒታልና በጦቁር አንበሳ ሆስፒታል ከሠላሳ አምስት ዓመት በላይ አገልግለዋል። በሥራ ጓደኞቻቸውና በተገልጋዩ ሕመምተኛ ሕዝብ ተቀርፆ የሚኖረው ተወዳጅነትን ያተረፉ ባለሞያ ሲሆኑ፣ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያው የሕክምና ሞያ "ዲን" ነበሩ። በሕክምና ሞያቸው ጤናን በሚመለከቱ ነጥቦች ያልተመራመሩት፤ ያልተሳተፉበት ሆስፒታልና ያልቃኙት የአስተዳደር ሞያ አልነበረም።

በሠላሳ አምስት ዓመት የአገልግሎት ዘመናቸው ውስጥ በያመቱ የአያሌ ሕዝብ ሕይወት ከሞት እንዲድን ረድተዋል። የሥራ ጓደኞቻቸውንና ረዳቶቻቸው ሁሉ፣ ስለ ከባዱ ሥራቸውና ሞያቸው አጋንነው ይመሰክራሉ። በየቀኑ አሥራ ስምንት ሰዓት ያገለግላሉ። የመኖሪያ ቤታቸው በልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል ቅፅር ግቢ ውስጥ ሆኖ፣— በየሰዓቱ በፅኑ ሕመም ለሚሠቃዩትና ለሕይወታቸውም አሥጊ በሆነ ሕመም ለሚጨነቁት ሕሙማን በማገልገል፣ ለዕረፍት ያልታደሉ ሐኪም ነበሩ።

በኮሚዩኒስቱ ደርግ ጊዜ ፕሮፌሠር አሥራት በጦር ሜዳ እንዲያገለግሉ ወደ ምፅዋ ወደብ ተላኩ። ይኸም የተፈጸመው ፕሮፌሠር አሥራት በጦር ሜዳ እንዲገደሉ ለማድረግ ነበር። በዚያን ጊዜ ደርግ ፕሮፌሠር አሥራትን "አድኃሪ" አሰኝቶ በጦር ሜዳ እንዲገደሉና በዚህም ሣቢያ "አድኃሪ" በሚል ሰበብ ሕዝቡን ለመጨፍጨፍ የታቀደ ዘዴ መሆኑ ግልፅ ነው።

ወያኔውም በአክራሪ ኮሚዩኒስትነቱ ፕሮፌሠር አሥራት የተነሱበትን ዓላማ ያደናቀፈ መስሎት አሥሯቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን አጠናክሮ፣ ጭቁንና ከበርቴ የሚባለውን መደብ ሠርዞ፣ ሕዝቡ በጐሣ እንዳይለያይ አስተባብሮ፣ የኢ.ህ.አ.ፓን አክራራ ኮሚዩኒስት አዲስ ሕገ መንግሥት ተፍቶታል።

የኢትዮጵያን አንድነት ለማረጋገጥ ኢትዮጵያዊ ደማችን እንደ ጐርፍ ይወርዳታል እንጂ፣ እንኳንስ ለወያኔ፣ ለፋሺስት ኢጣሊያ እንኳን ኢትዮጵያ አልተበገረችም።

በጐሣ አከፋፍሎ ለማለያየትና የኢትጵያንም አንድነት ገነጣጥሎ ለመበጣጠስ ያቀደውን አክራሪ የኢህአፓ ኮሚዩኒስት እናወድመዋለን። ፕሮፌሠር አሥራትም ከወህኒ ቤት ወጥተው የኢትዮጵያን ንፁሕ ዓየር በክብር የሚቀበሉበት ጊዜ ሩቅ አይደለም።

ከሕግ ውጪ የተበተነው ጽሑፍ

ይህ የተዛባ ሥነ ጽሑፍ ሰኔ 23 ቀን 1986 ዓም ተጽፎ ስለ ፕሮፌሠር አሥራት ከሕግ ውጪ መታሠር ለሠላማዊ ሠልፈኞች በካሣ ከበደ የጭን እመቤት አማካይነት ሲበተን የዋለ ነበር።

በንጉሠ ነገሥቱ ስም የተበተነው ይህ ጽሑፍ፣ በዘውድ ምክር ቤት በውል ያልተመረመረና ተዘጋጅቶም ለንጉሡ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ፣ ጽሑፉ የተዛባ ቃላት አዝሏል። ጽሑፉንም ለሠልፈኞቹ ትበትን የነበረችው ለዙፋን ምክር ቤቱ ሰብሳቢ ብታቀርብ፣ ወጊጅ አልቀበልም! ብለው አባረዋታል።

ንጉሠ ነገሥቱ የወያኔን አክራሪ ኮሚዩኒስት "በመንግሥትነት" አላወቁትም፣ ወደፊትም ሊያውቁት አይችሉም። ስለዚህም "የሽምቅ ጦር መንግሥቱ" ተብሎ ንጉሠ ነገሥቱ ያስተላለፉት በማስመሰል ንግሥቲቱ ከቢጤዎቻቸው ጋር ተመሳጥረው ያስበተኑት እትም ዋጋ ቢስ ነው። "ባንዲራ" ተብሎ የተጠቀሰውም ቃል ከኢጣሊያን ቋንቋ የተወሰደ በመሆኑ፣ ኢትዮጵያ የቋንቋ ድኃ ስላልሆነች ራሱን በቻለ "ሰንደቅ ዓላማ" መባሉን ይማሩት። ወያኔ "ብሔራዊ መንግሥት" ሊባል ስለማይችል ከዚህ በላይ እንደ ጠቀስነው ሁሉ፣ ንጉሠ ነገሥቱ መንግሥትነቱን አያውቁትም። "በመንግሥት ፖሊሲ ጉድለት" የተባለውም ንግሥቲቱ የወያኔን፣ መንግሥትነት አውቀውለት ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተወረሰው ገንዘብ እየፈነጠዙ ለመኖርና ንጉሠ ነገሥቱን ለማበሳጨት የተነሱበት ዓላማ መሆኑን የማያውቀው የለም።

"ለልዑል" እግዚአብሔር መፀለይ ተብሎ የተጠቀሰውም "ልዑል" የተባለውን ቃል ከንጉሣውያን ቤተ ሰብ ጋር ለማስተካከል የተመኙት ሲሆን፣ በአፄ ኃይለ ሥላሴ እንደበት እንኳን ይነገር የነበረው "ኃያሉ እግዚአብሔር" ይባል የነበረውን ተምረው ይታረሙ። "የሽግግር መንግሥት" "ሕገ ወጥ መንግሥት" "ይኸው መንግሥት" ተብሎ ለወያኔው አክራሪ ኮሚዩኒስት በንግሥቲቱና በአጃቢዎቻቸው በኩል የተሰጠው ስም፣ ከዚህ በላይ እንደ ዘረዘርነው ሁሉ የዘውድ ምክር ቤት ጽሑፉን አዘጋጅቶ ለንጉሠ ነገሥቱ በማቅረብ እንዲያፀድቁት ያላደረገው በመሆኑ የጽሑፉ አቀራረፅ በንጉሠ ነገሥቱ የዘውድ ምክር ቤት በኩል ፍጹም ተቀባይነት ያላገኘ መሆኑን ላገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እየገለጽን እናወግዛለን።

የታሪክ እንቅፋት

- ከሐምሌ (የታሪክ እንቅፋት) የቀጠለ -

ስለ ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ

የልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ ረዥም የሕይወት ታሪክ በመጽሐፍ ቅፅ ተዘጋጅቶ እስኪቀርብ ድረስ አስደናቂ ከሆኑት የታሪክ ዕንቅፋቶች ውስጥ አንደኛው መሆኑን ባጭሩ እንደሚከተለው ለማቅረብ እንሞክራለን።

አፄ ኃይለ ሥላሴ ከእቴጌ መነን የወለዷቸው የመጀመሪያይቱ ሴት ልጅ ልዕልት ተናኘ ናቸው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እቴጌ መነንን እንዲያገቡ ከልብ ይጥሩ የነበሩት ልጅ እያሱ ሚካኤል ነበሩ። የልጅ ኢያሱ ተቀናቃኝና የትምህርት ቤት ጓደኛ የነበሩት አፄ ኃይለ ሥላሴ እቴጌ መነንን ካገቡ በኋላ ልጅ ኢያሱ ለጥቂት ጊዜ ልባቸው አረፈ። የኋላ ኋላ ግን፣ አፄ ኃይለ ሥላሴ የልጅ ኢያሱን መንግሥት ገልብጠው ያዙ።

ንግሥት መድፈሪያሽ ወርቅ ለገንዘብ የሚያመልኩ፣ የኢትዮጵያ ርኃብና ትግል የማይሰማቸው፣ "እንደ ፈረንሣይቱ ንግሥት እንደ 'ማሪ አንቶኔት' ርኃብ ማለት ምንድነው ብላ በመጠየቅ ለምን "ኬክ አይበሉም" በማለቷ አብዮተኞች አንገቷን በሠይፍ ቆርጠው ዘውድን እርም በማለት የፈረንሣይን ሪፐብሊክ እንደ መሠረቱት" ካልተፈፀመ ንግሥት መድፈሪያሽ ወርቅ ሊገባቸው አይችልም። ልዕልት ተናኘ ደግሞ ከራሳቸው የተወለዱ ልጆችና አማቻቸው ልዑል ራስ መንገሻ ቶሎ ነግሠው ዙፋኑን እንዲይዙላቸው የሚጥሩ፣ በኋላም ከራሳቸው ቤት የተወለዱ ልጆች ብቻ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ዙፋንና ዘርዓ መንግሥት እንዲወርሱ ልጆቻቸውን አሠልፈው የሚገኙ ሁለቱም የታሪክ ዕንቅፋት ናቸው።

ደርግ በወህኒ ቤት ካጐራቸው ልዕልታት ውስጥ ልዕልት ተናኘ አንደኛዋ ሲሆኑ፣ ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ በምርምራ ጊዜ ለደርግ ይሰጡት በነበረው መግለጫ፣ "ቀን ቀን ጠቅላይ ሚኒስትር እኔ ነኝ፣ ሌሊት ሌሊት ግን ከአባታቸው ጋር የኢትዮጵያን ጉዳይ የሚወስኑት ጠቅላይ ሚኒስትር ልዕልት ተናኘ" ናቸው ያሉት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የታሪክ ዕንቅፋት ማስረጃ ሆኖ ይኖራል። ከአፄ ኃይለ ሥላሴ በፊት የነበሩት ጥንታውያን ነገሥታቶቻችን፣ ቤተ ርስት ወይም ርስተ ጉልት የሚባል ዕድፍ ሳይበክላቸው በክብር አልፈዋል።

ከዚህ በላይ እንደ ተጠቀሰው ሁሉ፣ የአያታቸው የልዑል ራስ መኰንንና የአፄ ምኒልክ ርስት አልባ ሆኖ መኖር በንፁሑ ታሪካቸው እየታወቀ፣ ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ በቤተ ርስት ላይ ያላቸው እምነት የጋለ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

ልዑል ራስ መኰንን ርስት የሚባል ነገር አልነበራቸውም። የመኖሪያ ቤታቸው የነበረው፣ በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ የሆነው ነበር። የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥ የነበሩት ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ፣ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ለመገልበጥ ሙከራ ካደረጉ በኋላ፣ ባለሥልጣኖቹን በዚሁ ቤተ መንግሥት አረንጓዴ ሣሎን ውስጥ ፈጅተው፣ እሳቸውና ወንድማቸው ገርማሜ ንዋይ፣ ሌሎችም የዓላማው ተከታይ ክብር ዘበኞች በስቅላት መሥዋዕት ሆነዋል። ልዑል ራስ መኰንን ደግሞ ቤተ ርስት የሚባል ሳይበክላቸው ከዚህ ዓለም በሞት አልፈዋል። ይኖሩበት የነበረውም ቤት ከታህሣሥ 5 ቀን 1953 ጀምሮ ዩኒቨርስቲ ሊሆን ችሏል። ታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳኛው ምኒልክ ቤተ ርስት ቀርቶ፣ አንዲት ጋሻ ርስት ያልነበራቸው በሕዝቡ ዘንድ ተደናቂ መሪ ነበሩ። በጦር ሜዳ ይዋደቅ ለነበረው ጀግና የታሪኩ [illegible] ዘንድ ጋሻ መሬት ይሰጡት ነበር። የግል ርስት እንዲኖራቸው መኳንንቶቻቸው ስብሰባ አድርገው ቢመክሩዋቸው፣ "ኢትዮጵያ በሙሉ የማን ሆና ነው፣ ለኔ የተለየ ርስት የሚኖረኝ? ይሉ

ወደ ገጽ 4 ይዞራል

ከገጽ 3 የዞረ

የነበሩት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት" ዳኛው ምኒልክ የኢትዮጵያ ታሪክ ባለቤት ናቸው።

ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ በቤተ ርስት ላይ ያላቸው እምነት የጋለ መሆኑን ለመግለፅ ሲሆን፣ አምስት ሺህ ዘመናት ኢትዮጵያን በነፃነት ያቆዩ ነገሥታት ከሚኖሩበት ቤተ መንግሥት በስተቀር ቤተ ርስት የሚባል ነገር በታሪክ አላቆዩም። ልዕልት ተናኘ ግን፣ አያታቸው ልውል ራስ መኰንን በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የፈረንሣይ የምድር ባቡር ወደ አዲስ አበባ ሲገባና "ሰባራ ባቡር" በተባለው ሠፈር ቆሞ እስከ ቀረ ድረስ ያለውን ታሪክ ለጥቅማቸው ማስታወስን ሥራዬ ብለው ተያያዙት። ልውል ራስ መኰንን በዚያን የመጀመሪያው ባቡር ተሣፍራው የተጓዙባት አገርና መሬት ሁሉ ጠቅላላ አገር ርስትነቱ ለኔ ይገባኛል ብለው ለአባታቸው ለአፄ ኃይለ ሥላሴ በመንገር ጨርጨርን እስከ "አሰቦት ገዳም" ድረስ በርስትነት ያዙ። ከዚህም በኋላ ለኢጣያሊያን ኩባንያ በኮንትራት ሰጥተው ሕይወታቸውን ሲቀጩ የኖሩ እመቤታችን ናቸው።

ሟቹ ባለቤታቸው ቢትወደድ አንዳርጋቸው መሣይ ደግሞ፣ በኢትዮጵያ ክፍላተ አገሮች ውስጥ የነበረውን የኢጣሊያን የእንዱስትሪ ዕቃዎች ሁሉ፣ በሥልጣናቸው ዘርፈውና ለእንግሊዝ በመሸጥ የከበሩ ጌታ ነበሩ። በዚህም የጐደፈ ታሪካቸው ለኢትዮጵያ ክፍላተ አገር ሕዝብ ደም መፋሰስ ጠንቁ ቢትወደድ አንዳርጌና ልዕልት ተናኘ መሆናቸውን ታሪክ አይዘነጋውም።

ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ ደርግ ከገደላቸው ከሟቹ ከደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃም ጋር ምሥጢር የሆነ የግል ግንኙነት ነበራቸው። ደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃም ደሞ፣ የአፈወርቂ አብርሃም ወንድም ናቸው። ኢሣይያስ አፈወርቂ ዛሬ የኢትዮጵያና የኤርትራ ፕሬዚዳንት ሆኖ፣ መለስ ዜናዊን እንደ ፈለገው ሲያሽከረክረው እናየዋለን። ኢሣይያስ አፈወርቂ የቻይናው ማኦ ሴቱንግ አክራሪ ኮሚዩኒስት ርዕዮተ ዓለም ተከታይ ሆኖ ቻይና ውስጥ በማርክሲስትነት የተጠመቀ እንደ ነበረ ታሪክ ይመሰክራል። ኢሣይያስ አፈወርቂ የደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃም የወንድም ልጅ ሲሆን ልዕልት ተናኘ ደግሞ በደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃም አማካይነት፣ ስለ ኤርትራ መገንጠል ብዙ ሚና ተጫውተዋል። ከነዚህም ሚናዎች መካከል የሚከተለውን ሐተታ በማስረጃነት ልናቀርበው እንገደዳለን።

አፄ ኃይለ ሥላሴ በዙፋናቸው ላይ እንዳሉ፣ ኢራንና ኢራክ ውስጥ፣ "በኮማንዶ" ሥራና ሙያ የሠለጠኑ ኤርትራውያን በኬንያ በኩል አዲሱን የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሕንፃ ለማፍረስ ወደ ኢትዮጵያ ሊገቡ ማቀዳቸውን የኢትዮጵያ የስለላ ድርጅት ደረሰበት። ይህ የስለላ ድርጅት ኬንያ ውስጥ የነዚህን የኤርትራውያን ኮማንዶዎችን ተንኰል ሲከታተል፣ ብዙ የፈንጂ መሣሪያዎች ማዘጋጀታቸውን አረጋገጠ። ክትትሉን ቀጥሎ አዲስ አበባ ሲገቡ አብሮ ገባ። በመጨረሻውም ኮማንዶዎቹ ፈንጂውን ሁሉ ጭነው ደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃም ቤት መግባታቸውን ተከታትሎ በማየት አረጋገጠ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ኮማንዶዎች በስለላ ድርጅቱ መሪነት ከነፈንጂዎቻቸው ተይዘው ታሠሩ። የስለላው ድርጅት ደጃዝማች ሰሎሞንን እጅ ከፍንጅ ለመያዝ ቤታቸው ሲገባ ልዕልት ተናኘ ወርቅ ለአባታቸው ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ነገረው ደጃዝማች ሰሎሞን አብርሃም እንዳይታሠሩ፣ የተያዙትም ወንጀለኞች በሙሉ እንዲለቀቁ አደረጉ። ከዚህ የበለጠ ወንጀል ከልዕልት ተናኘ የሚጠበቅ ምን ነገር ይኖራል?

ፀሐፌ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ የተንገፈገፉት በዚህ ዓይነት የወንጀል ሥራና የታሪክ ዕንቅፋትነታቸው ነበር። ልዕልት ተናኘ በዘርና በዙፋን ላይ ያላቸው እምነት ተነገሮ አያልቅም።

ሟቹ ልጃቸው ኰማንደር እስክንድር ደስታ ደርግ የአፄ ኃይለ ሥላሴን ዙፋን ሲገለብጥ፣ አምልጦ ወደ ጂቡቲ ገብቶ ነበር። ልዕልት ተናኘ ራሳቸው እየጐተጐቱ ወደ አዲስ አበባ ባስቸኳይ እንዲመጣ አድርገው አስገደሉት። የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ አራተኛ ክፍለ ጦር ዕሥር ቤት መኘታችን ጐን ለጐን ስለ ነበር፤ በሕይወት እስካለ ድረስ ብዙ እንወያይ ነበር። የኰማንደር እስክንድር ሞት እስካሁን ያሳዝነኛል።

ልዕልት ተናኘ ግን ሟቹ ልጃቸው ኰማንደር እስክንድር ደስታ ወንድ ልጃቸው እሱ ብቻ ስለ ነበር፣ የአፄ ኃይለ ሥላሴን ዙፋን እንዲወርስ ከፍተኛ ምኞት ነበራቸው። ነፍሰ ገዳዩ ደርግ ከሕግ ውጭ የኰማንደር እስክንድርን ንፁሕ ደም በማፍሰስ ለጊዜው የረካ ቢመስለውም፣ ጊዜውን ጠብቆ በቆፈረው ጉድጓድ የሚገባበት ወቅት ሩቅ አይሆንም። ልዕልት ተናኘም በኰማንደር እስክንድር በኩል የነበራቸው ምኞት ሳይሳካላቸው ቀረ።

ልዕልት ተናኘ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር ወደ እንግሊዝ አገር መሰደዳቸው ይታወሳል። በዚሁ የስደት ዘመናቸው ጊዜ ቋንቋ መማር አስፈላጊያቸው ስለ ነበረ፣ ቀደም ሲል ለትምህርት ወደ እንግሊዝ አገር ተልከው የነበሩት ክቡር አቶ አበበ ረታ በኋላ የሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር የሆኑት እንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲያስተምሩዋቸው ተደረገ። በሁለቱ መካከል በነበረው ግኙነት ክቡር አቶ አበበ ረታ አንዲት ሴት ልጅ ከልዕልት ተናኘ ወለዱ። ይህችም ሴት ልጅ ሥዩም ሐረጐትን አግብታ ስትኖር፣ ደርግ የመኖሪያ ቤቷን ከቦና ተኩስ አስከፍቶ ገደላት። መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ይህ አልበቃ ብሎት፣ የደርግ አባላት በሙሉ ድምፅ አቶ አበበ ረታ ሞት አይፈረድባቸውም ብለው ቢወስኑ፣ ከልዕልት ተናኘ ልጅ የወለዱ በመሆናቸው ብቻ መሞት አለባቸው ብሎ ገድሏቸዋል። ክቡር አቶ አበበ ረታ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ምሑራን የመጀመሪያው ሊቅ ነበሩ።

በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ልዕልት ተናኘ የሰማንያ ዓመት "ታሪክ አልባ" ዕድሜያቸውን አሜሪካን አገር "በማሪዮት ሆቴል" አክብረው ሲውሉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረኃብ አለንጋ እየተገረፈ፣ ያባታቸውም አፅም የክብር ቦታውን ሳይዝ፣ አዝማሪ አቋመው ሴት ወይዘሮ ሁሉ፣ ግጥም ለመስጠት ሲሽቀዳደም ለጉድ ይታይ ነበር።

አፄ ኃይለ ሥላሴ ካወረሷቸው የስዊስ ባንክ ሂሳብ የሚበቃቸውን ያህል ገንዘብ አውጥተው ወደ አሜሪካን አገር ተመልሰው ለመግባት ሲሞክሩ፣ ትንሽ የኢሚግሬሽን ችግር ገጠማቸው። በአሜሪካ ውስጥ ለጊዜው የመኖሪያ ፈቃድ ስላልነበራቸው ወደ እንግሊዝ አገር ለመግባት ተገደዱ። ከዚያም በአሜሪካን ኤምባሲ አማካይነት ወደ አሜሪካ ተመልሰው ለመግባት ቻሉ።

የልዕልት ተናኘ የዙፋን ምኞት አሁንም አላቋረጠም። ልዕልት ዓይዳ ደስታ የልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ባለቤትና የብዙ ልጆች እናት መሆናቸው ግልጽ ነው። ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ደግሞ በኔ በኩል የዘውድ መንግሥት አልፈልግም እያሉ፣ የወያኔን ኮሚዩኒስት በመገዝገዝ ላይ ይገኛሉ። የልዕልት ተናኘ ዋና ጥረት ልዑል ራስ መንገሻ እንዲነግሡና ዘውዱ ለልዕልት ዓይዳ ልጆች እንዲወራረስላቸው ብቻ ነው።

ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም "ኢዲዩ" ለተባለው ድርጅት ከጄኔራል ኢያሱ መንገሻ ቀምተው፣ መዋቅሩን ለራሳቸው ጥቅም እንዳዋሉት ታሪክ ይመሰክራል። ይኸንንም ያደረጉት የዘውድን መንግሥት ለመመሥረት ተደራጅቶ የነበረውን "የኢዲዩ" ጦር በማፍረስ፣ "ከኢህአፓ" ጋር ተመሳጠሩ። ከዚህ በኋላ የራሳቸውን "የኢዲዩ" ጦር አደራጁ። ቀጥሎም "ከኢህአፓ" ጋር ሆነው ቢትወደድ አዳነን አስገደሉ። ይህ ብቻ ስላላረካቸው ከጀግናው ቢትወደድ አዳነ ጋር አርበኞች የነበሩትን ሁሉ አሠሩዋቸው። አሁን ደግሞ በቅርቡ ልውል ራስ መንገሻ ሥዩም ካሊፎርኒያ ውስጥ የራሳቸውን ተከታዮችና "የኢህአፓ" ተወካዮች በአንድነት ተሰብስበው ንግግር ሲለዋወጡ መዋላቸውን ሰማን። ይህ ሁሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ነግሦ የሚገኘውን የወያኔ አክራሪ "የኢህአፓ" ድርጅት ተባብረው ማቀፋቸውንና ወደ ፊትም አገሪቱን ለማጥፋት ያቀዱ መሆናቸውን ያስረዳል። ያም ሆነ ይህ የራሳቸውን "የኢዲዩ" ጦር ሲመሠርቱ፣ "ከኢህአፓ" አክራሪ ኮሚዩኒስት ጋር በአንድነት ተባብረው የመሠረቱት ስለሆነ ዛሬ የዘውድ መንግሥት ለመመሥረት አቅቷቸው በችግር ላይ ይገኛሉ። ልዕልት ተናኘም ሌላ ዘዴ ስላጡ፣ የአፄ አምኃ ሥላሴን ዙፋን ለማደናቀፍ ይጥራሉ።

ከዚህ በስተቀር ልዕልት ተናኘ ከንግሥቲቱ ጋር እየተመሳጠሩ የንጉሡን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወደ ውጪ በላኩበት ወቅት የሹም ሽር ናዳ ቤት ለቤት ያሳውጁ ጀመር። ይኸንንም ለማስረዳት ያህል ልዕልት ተናኘ ከልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ ጋር ተመሳጥረው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወነጀሉት አይዘነጋም። በዚያ ሁሉ ዘዴ ንጉሡ ብቻቸውን ሲቀሩ ልዕልት ተናኘ በንግሥቲቱ ደጋፊነት የራሳቸውን የዘውድ ሥልጣን ለማመቻቸት በቂ ዘዴ ያገኙ መሰላቸው። ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝብ የዚህን ዓይነት ራስን የማታለል ዘዴ ከመናቅ ቦዝኖ አያውቅምና የኢትዮጵያውያንን ታላቅነትና ብልህነት ቢገነዘቡት ይሻላቸው ነበር።

ይህም አልበቃ ብሎ አሁንም ልዕልት ተናኘ የአፄ አምኃ ሥላሴን የስደት መንግሥት ለማፍረስና መሠረቱን አናግተው ወደ አማቻቸው ዙፋኑን ለማዛወር ታጥቀው ተነሡ። ከለንደን ጀምሮ እስከ ዩናይትድ ስቴትስ በትክክል ሥራ ላይ የዋለውን የንጉሠ ነገሥቱን የዙፋን ሥራ በማከናወን ላይ የሚገኘውን የዙፋን ምክር ቤት ከልዕልት ዓይዳ ደስታ ጋር ተመሳጥረው ንግሥቲቱ እንዲፈርስ አደረጉ። የአፄ አምኃ ሥላሴን የዙፋን ምክር ቤት ባለሥልጣኖችና ምሑራን ሁሉ እንዲገለሉ በማድረግ ልዕልት ተናኘ የራሳቸውን የዙፋን ምኞት ለመዘርጋትና ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩምን ለማንገሥ በከባድ ጥረት ላይ ይገኛሉ። ልዕልት ዓይዳ ደስታም ልጆቻቸው ዙፋን እንዲወርሱ ለማድረግ አፄ አምኃ ሥላሴን በሕይወት ሊገድሏቸው ተመኙ። ይህ ሁሉ እንዲሳካ ልዕልት ተናኘ ለልጆቻቸው ሁሉ፣ ከስዊስ ባንክ ካወጡት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የውርስ ገንዘብ ለያንዳንዳቸው አንድ አንድ መቶ ሺህ ዶላር አከፋፍለዋቸዋል።

በቤተ መንግሥቱ አካባቢ የሚካሔደውን የተንኰል ሥራዎችና የታሪክ ዕንቅፋት ሕዝቡ ይፍረደው። በተለይም የኢትዮጵያ የሃይማኖት መሪዎች ሁሉ እንዲመካከሩበት አጥብቀን እንጠይቃለን። ልዑል ራስ መንገሻና ልዕልት ሰብለ ደስታ የዙፋኑን መዋቅር ወደ ራሳቸው ለማዛወር አዲስ አበባ ከርመው ዛሬ ይኸንኑ ጉዳይ ፍጻሜ ለማድረስ ወደ አሜሪካን አገር ተመልሰው ገብተዋል። ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ ደሞ ዙፋኑን ወደ ልዕልት ተናኘ ቤት ለማዛወር በትግል ላይ ናቸው።

የልዕልት እጅጋየሁ ልጆችና የልዑል መኰንን ልጆች ወደ አፄ አምኃ ሥላሴ ቤተ መንግሥት እንዳይደርሱና በሐሳብ እንኳን ንጉሠ ነገሥቱን እንዳይረዱ የታሪክ ዕንቅፋት ሆነውብናልና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዛሬ ጀምረህ ከወራሴ መንግሥቱ ዙፋን ጐን ቁመህ ባገር ወዳድነት ለኢትዮጵያ አንድነት ተጋደል እያልን ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ጊቹ የኢራት ሻህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወዳጅ ስለ ነበሩ፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ ላገራቸው ዙፋን በጦር እንዲታገሉ አትደው፣ ሻሁ ብዙ ሚሊዮን ዶላር ለልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን እንዲከፈል አደረጉ= ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ለልዑል አልጋ ወራሽ እንዲሰጥ የታዘዘውን ገንዘብ በኪሳቸው አግብተው ጥቂት ዶላር ለአንዳንድ የኢዲዩ አባላት ካከፋፈሉ በኋላ፣ ጠቅላላውን ገንዘብ ይዘው በትግራይ ውስጥ ጦር አቋቋሙ= ልዑል ራስ መንገሻ ያቋቋሙትን የኢዲዩ ጦር፣ አክራሪው የኢህአፓ ኮሚዩኒስት ከአሲምባ ወጥቶ አወደመው።

ቀጥሎም የልዑል ራስ ሥዩም መኳንንቶች የነበሩትን ሁሉ እየተከታተሉ ፈጇቸው= አሁን ደሞ አዲስ አበባ ውስጥ ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም "ለኢትዮጵያ ዘውድ አያስፈልጋትም" እያሉ ምናልባት ወያኔ "ይራበሽና" እርስ በርሱ ተጋጭቶ፣ ዘውዱን አጥራ ከምድር አንስታ፣ ከሰማይ ላይ ስትጥልልኝ፣ እኔ ድሞ "ቀልቤ" በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ "ቂጥ" እላለሁ ብለው በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ=

ከዚህም ሌላ፣ የጀርመኑ ጥንታዊ የነገሥታት ዘር ወገኖች ብዙ ገንዘብ በባጀት ወስነው፣ የኢትዮጵያ የዘውድ ወገኖች ተቃራኒውን በጦር ኃይል እንዲገጥሙ የሚያፈሱትን ገንዘብ ልዑል ራስ መንገሻ ገንዘቡን እየተቀበሉ ይጠቀሙብታል= ይኸው የጀርመን ነገሥታት ዘርፍ ለሚቹ ልዑል ዳዊት መኩንን ይከፍለው የነበረውን ገንዘብ፣ ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ለጀርመን ጥንታዊ ዙፋን ድርጅት አስረድተው መረከብ ከጀመሩ ጥቂት ዘመናት አልፈዋል= እንዲያውም ሚቹ ልዑል ዳዊት ወደ ሱዳን አገር ሔዶ በነበረ ጊዜ ልዑል ራስ መንገሻ ለደርግ አሳልፈው ሊያስረክቡት ፈልገው ሳይሳካላቸው ቀረ። የጀርመኑ የነገሥታት ድርጅት ለልዑል ዳዊት መኩንን ይከፍል የነበረውን ከፍተኛ ገንዘብ ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ከደርግና ከወያኔ ጋር ጦር የሚያካሒዱ አስመስለው የሚያገኙት ባጀት ከፍተኛ መሆኑን ከዚህ በላይ ጠቅሰናል= የዚህ ሁሉ መዘዝ የልዕልት ተናኘ ጠንቅ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል።

ልዕልት ተናኘ በጋብቻ ሁሉ እየገቡ ብዙ ዘዴ ሲፈጥሩ የኖሩ የታሪክ ዕንቅፋት ናቸው። ወንድማቸው ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ልዕልት ወለተ ዕሥራኤል ሥዩምን እንዲያገቡ ያደረጉ እሳቢ መጣይ ነበሩ= ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ደግሞ ልዕልት ተናኘ የባላቸው የራስ ደስታ ዳምጠውን የወንድም ልጅ ማለት፣ የሜጀር ጄኔራል አበበ ዳምጠውን ልጅ ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበን ለልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ደሴ ከተማ ድረስ ወስደው አቀረቡ።

የዚህ ሁሉ ጠንቅ የዘውድ መንግሥት ልዕልት ተናኘ ወደሚገኙበት አቅጣጫ ሩቁን እንዲያዞር ነበር= ሆኖም የልዕልት ተናኘ ምኞት በኢትዮጵያ ዘውድ ላይ ብዙ ሚና ተጫውቷል= ይህ ሁሉ ሲደረግ የኖረው በአፄ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ ዝንጋታ እንጂ፣ በልዕልት ተናኘ ብልህነት አልነበረም=

የፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድም እስከ ሞት ድረስ መሥዋዕት መሆን፣ የልዕልት ተናኘን የታሪክ ዕንቅፋትነት ሲያጋልጥ ይኖራል እንጂ የልዕልት ተናኘን ብልህነትና ብልሃት የሚያንፀባርቅ አንዲት መሥመር እንኳን ታሪክ ለማግኘት ዕድል አይኖረውም=

ይቀጥላል........

ልዑል ራስ መንገሻና የትግራይ ድርጅቶች

"ኢህአዴግ፣ ሕወሓት፣ ኢህአፓ፣ ኢዲዩ" የተባሉት ድርጅቶች የተሟሩት ትግራይ ውስጥ ሲሆን፣ የኢህአዴግ አንዱ ክንፍ በልዑል ራስ መንገሻ የሚመራው ኢዲዩ ነው= ምሥረታውም ትግራይ ውስጥ እንዲሆን ያደረጉት ልዑል ራስ መንገሻ ናቸው=

ፕሬዚዳንትነቱን፣ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን፣ የመከላከያ ሚኒስትርነቱንና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ቁልፍ ቦታዎች የትግሬ ተወላጆች እንዲይዙላቸው ያደረጉትም ሌላው ድርጅት እንዳይገባ ለማገድ ነው። ጦሩም በአሲምባ ተራራ የመጣ የኢህአፓ ድርጅት መሆኑ ግልጽ ነው። ስሙን ለመለወጥ በተደረገው ማታለያ "ኢህአዴግ" ብለውታል። ከዚህም አልፈው ሁሉንም ያቀፈ ለማስመሰል "ቅንጅት" ብለውታል። ከዚያም ቅንጅት ኢድሐቅ ብለው አሻሽለውታል። ይህ ሁሉ መሻሻል የተደረገው የተከፋፈለውን ድርጅት አንድ ለማድረግ ነበር።

ኢድሐቅን ሲመሠረቱ ኢዲዩ መሥራች አባል ሆኖ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ይህ ብቻ ሳይሆን ኢዲዩ በልዑል ራስ መንገሻ አማካይነት የወያኔውን የሽግግር መንግሥትነት አውቆና ተቀብሎ ውሳኔ ሰጥቶበታል። ኢድሐቅም ከኢዲዩ ጋር በጉዳዩ ተስማምቶበታል።

በሚያዝያ 1985 ተደርጐ በነበረው ስብሰባ በኢህአዴግ የግል ውሳኔ ብቻ አብዛኛውን የምክር ቤት መቀመጫ ለራሳቸው ብቻ እንደ ያዙት ተረጋግጧል። ሌሎቹ ድርጅቶች ግን ከዲሞክራሲ አፈጻጸም ውጪ አስገድደው የሰጧቸውን ቢቀበሉም፣ ለውሳኔ የሚቀርበውን የድምፅ ብልጫ አስቀድመው የወሰኑት ስለ ሆነ ዲሞክራሲን የገደሉት መሆኑን እንዲያውቁት አስረድተዋቸዋል።

ልዑል ራስ መንገሻ ዘውድ ለኔ ይገባኛል የሚሉ መሆናቸውን በአንዳንድ መጽሔት ተጠይቀው፣ ከተሠለፉበት የኢዲዩ ዓላማ ጋር የማይስማማ መሆኑንና፣ ራሳቸውም በዚህ ሐሳብ ተመርተው የማያውቁ መሆናቸውን በመግለፅ፣ ዘውድን አልቀበለውም ሲሉ ተቃውመዋል።

የኢዲዩ ድርጅት በመጀመሪያ የተቋቋመው ለንደን ላይ ሲሆን ድርጅቱንም በመጀመሪያ ያቋቋሙት አፄ አምኃ ሥላሴ ናቸው። ልዑል ራስ መንገሻ ስለ ሞዓ አንበሳ ተጠይቀው "በኮንስቲቱዩሽናል ሞናርኪ" የሚመራ መሆኑን የገለፁት ትክክል አይደለም። ሞዓ አንበሳ ከነገሥታት ጋር አብሮ የተወለደና ያደገ ሲሆን፣ ኮንስቲቲዩሽናል ሞናርኪ" ዘመናዊ ሥርዓቱ ነው። የሞዓ አንበሳ ድርጅት ራሱን የቻለ የዘውድ አካል ሆኖ የሚመራ ነው።

የሕውሐት ድርጅት "ማርክሳዊ ሌኒናዊ" ሲሆን፣ ደርግን ለመጣል ግን፣ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን እደግፋለሁ ብሎ ለአሜሪካኖች በማጒንበስ ደርግን ሊጥል ችሏል። የደርግን መውደቅ ስንደግፍ፣ ለሌላው አክራሪ ማርክሲስት ልንንበረከክ አንችልምና አገር ወዳድ ሁሉ አንድነቱን አጠናክሮ የልዑል ራስ መንገሻን ወያኔ በመዋጋት፣ ከኢትዮጵያ ዙፋን ባስቸኳይ እንዲያወርደው የሞት የሽረት ግዴታው ይሆናል።

ስለ ኢዲዩ ድርጅት

ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩምና ጄኔራል ኢያሱ መንገሻ የኢዲዩን ታጋይ አርበኛ ማነቃቃት ሲገባቸው ለትግሉ አስፈላጊ የሚሆነውንና በምርኮ ተገኝቶ በእጃቸው የሚገኘውን ለመግለጽ ሳይፈልጉ ቀሩ። በሌላም በዕርዳታ የሚገኘውን መታገያ ሁሉ ለታጋይ አርበኛ ማቅረብ ሲገባ ይኸንን ባለመፈጸማቸው ቢትወደድ አዳነ መኰንን ሥልጣኔን ለቅቄ ገለልተኛ ሆኛለሁ አሉ። በዚህ ምክንያት ምክትላቸው የነበሩት ልዑል ራስ መንገሻ ዋና ሊቀ መንበር ሆነው ተሾሙ። ልዑል ራስ መንገሻ ታጋዩን አነቃቅተው የመታገያ ኃይል እንዲያቀርቡ ለብዙ ዓመታት ተጠበቁ። ካርቱም ውስጥ



ራስ ቢትወደድ አዳነ መኰንን - 5 ዓመት አርበኛ፣ ደርግንም የተቋቋሙ አርበኛ በወያኔው ኢህአፓና ኢዲዩ የተገደሉ ሲሆኑ፣ ወደፊት የሞዓ አንበሳ አርበኞች ይፋረዷቸዋል።

ተቀምጠው በስም ብቻ ሊቀ መንበር ነኝ ከማለት በስተቀር በተግባር የሚያሣዩት ውጤት ጠፋ። በኢትዮጵያ አርበኞች ደም ከደርግ ጦር ተማርኮ የነበረውንና ከሺ አምስት መቶ በላይ የሆነው ከባድ መሣሪያና ጠብመንጃ ሁሉ በሱዳን ጦር ተወሰደ። ይኸም ሊሆን የቻለው ጦሩ ሱዳን ጠረፍ እንዲቀመጥ በማድረጋቸው ነበር። ከዚህም በኋላ ታጋይ አርበኛ ሊበታተን ቻለ። ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላም ብዙ ጉድለቶች ነበረባቸው። ዋና ሊቀ መንበር የነበሩትም ቢትወደድ አዳነ ሥልጣኑን በገዛ ፈቃዳቸው ስለ ለቀቁ አርበኛው አልተደሰተም ነበር። ትግሉን ያዳከሙት ልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም በ1974 ከሥልጣን ተወገዱ። ከዚህ በኋላ አርበኛው አርባ አምስት የሸንጐ አባላትና ሃያ አምስት የኮሚቴ አባላት መርጦ ትግሉን ቀጠለ። ቀደም ሲል በልዑል ራስ መንገሻ ሥዩም ላይ የተሰጠውን የሥራ ዕገዳ ኮሚቴው አፀናው። በዲሞክራሲ ለሚያምኑት ዓለማት ኤምባሲዎች ሁሉ የትግሉ እምነት ተላለፈ። በገዳሪፍና በትዋናናሪቭ ያሉት ኢትዮጵያውያን በሙሉ አርባ አምስት ገጽ በያዘ ፊርማቸው ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ እንዲመሩት ጠየቀ። የአርበኛውን ሕዝብ ጥያቄ ክቡር ደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ደስታ ለልዑል አልጋ ወራሽ እንዲያቀርቡ አርበኛው በሙሉ ድምጽ ተስማማ። ክቡር ዳጃዝማች ብርሃነ መስቀል ደስታ ጠቅላላው አርበኛ ተስማምቶ የተፈራረመበትን እንግሊዝ አገር ወስደው ለንጉሠ ነገሥቱ አስረከቡ። ንግሥቲቱ ደግሞ የአርበኞቹን የጋለ ስሜት የተሞላበትን ጽሑፍ በምሥጢር አሳልፈው ለራስ መንገሻ ሥዩም ሰጡ። ልዑል ራስ መንገሻም በዚሁ ጽሑፍ ሳቢያ ከኢህአፓ አክራሪ ኮሚዩኒስት ጋር ተመካከሩ። ጀግናውም የኢትዮጵያ አለኝታ ቢትወደድ አዳነ መኰንን በዚሁ ሳቢያ ተገደሉ። ቁጥራቸው ያልታወቀ ብዙ የአርበኞች መሪ የነበሩትም ጀግኖች ሱዳን ውስጥ የት እንደደረሱ ሳይታወቅ ቀረ።

ሕግ ጠቀስ ደብዳቤ

(ከአፈንጉሥ ተሾመ ኃ/ማ)

የዘውድ ምክር ቤቱን መመሪያና ትእዛዝ በመከተል ለመስራት ያልተቻለበትን ምክንያት በመግለጽ አፈንጉሥ ተሾመ ኃይለ ማርያም ለአፄ አምኃ ሥላሴ የጻፉትን ህጋዊ ደብዳቤ እናቀርባለን። ጽሑፉም የተገኘው ከንጉሠ ነገሥቱ ጽ/ቤት ሲሆን አፈንጉሥ ተሾመ ኃይለ ማርያም ቀደም ሲል በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በልዩ ልዩ ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን ላይ የነበሩ ናቸው።

በዩናይትድ ስቴትስ የኢዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አምባሳደር ሆነው አገልግለዋል። በመጨረሻውም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት አፈንጉሥ ሆነው ከፍተኛ አገልግሎት በመፈጸም ፍትሕ አስገኝተዋል። ይኸም ከዚህ ቀጥሎ ለንጉሠ ነገሥቱ የተጻፈው የአፈንጉሥ ተሾመ ሕጋዊ ደብዳቤ ለኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ሕዝብ ሕጋዊ መመሪያ ሆኖ በታሪክ አምድ ይመዘገባል። ለኢትዮጵያውያን የሕግ ተማሪዎችም እጅግ ጠቃሚ እንደሚሆን በማመን ቃላቱን በሙሉ እንደሚከተለው አትመነዋል።

ግርማዊ ሆይ!

ግርማዊነትዎ ባደረጉልኝ ጥሪ መሠረት ጥሪዎን ተቀብዬ ትእዛዝዎን አክብሬ እስካሁን ድረስ በተቻለኝ መጠን በቅን ሳገለግል ቆይቻለሁ። የግርማዊነትዎን መመሪያና ትዕዛዝ ተከትዬ ሳገለግል በቆየሁበት በዚህ አንድ ዓመት በላይ ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገር ለማየትና ለመረዳት አንዳንድ ግምቶችንም ለመውሰድ ዕድል አግኝቻለሁ።

ግርማዊ ሆይ

እንደሚታወቀው ዘውድ የአንድነታችን ምልክት በመሆን የጎሣ የዘር ወይም የሃይማኖት ልዩነት ሳያደርግ ሁሉንም ወገን በማቀፍ

ወደ ገጽ 6 ይዞራል

ከገጽ 5 የዞረ

የኢትዮጵያን ሕዝብ አዛምዶና አስተባብሮ የኖረ ታሪካዊ ቅርሳችን ነው። በዘውዱ ወግና ሥርዓት መሠረት ሕዝብ ይደልዎ (ይገባዋል) ብሎ በተቀብዖ ዘውድ ጭነው ሃላፊነት የተቀበሉ ነገሥታት አባቶችም ሁሉ ከጥንት ጀምሮ ለአገራቸው ዕድገትና ብልፅግና ለሕዝባቸው ደህንነት ታላላቅ ሥራዎች ፈፅመዋል የኢትዮጵን አንድነትና ሉዐላዊነት ለማስከበር ከፍተኛ መስዋዕት ከፍለዋል። የግል ጥቅም ሳይፈልጉ ወይም ከሕዝብ የተለየ ዕድል እንዲኖራቸው ሳያደርጉ ከሕዝባቸው ጋር አንድ አካል አንድ አምሳል ሆነው በመተሣሠር ሕዝቡን አሰባስበው በአንድነት እንዲቆም በማድረግ ኢትዮጵያን አስከብረውና ጠብቀው አቆይተዋል። በዚህ ሥራቸው ፅላት ተቀርፆላቸው በስማቸው ገዳም ተሠርቶላቸው ቅዱስ እየተባሉ ሲጠሩ የሚኖሩ እንዳሉ የታወቀ ነው።

የግርማዊነትዎም ፍላጎትና ምኞት የሚያደርጉትም ጥረት ሁሉ የአባቶችዎን ፈለግ በመከተል ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዐላዊነት መከበር ለሕዝብ መብት መረጋገጥ ለሰላም ለፍትሕና ርትዕ መስፈን በጠቅላላው ለአገር ዕድገትና ብልፅግና የሚቻለዎን ሁሉ ለማድረግና የሚፈለግብዎን መስዋዕት መሆኑን በቅርብ ሆኜ በማየት ተረድቻለሁ።

ግርማዊነትዎ የሕዝቡን ኑሮ ለመኖር እንጂ የተለየ ኑሮ አይሹም። የግል ጥቅም ፈላጊ አይደሉም ለኢትዮጵያ ክብርና ለሕዝቡም ደህንነት የሚጨነቁ በኢትዮጵያ ሰላም ተገኝቶ የሕዝቡ ሙብት በእኩልነት ተከብሮና ተጠብቆ የሚኖርበት ፍትሕና ርትዕ የሰፈነበት ሥርዓት እንዲዘረጋ የሚጥሩ አርቆ አስተዋይ አሳቢና አመዛዛኝ የሆኑ ትልቅ መሪ ነዎት። እስካሁን ያልተለየሁዎት የዚህ ዓይነት የትልቅነት ባህርይ ያለዎት መሆኑን በማየቴ ነው። የግርማዊነትዎን ማንነት ለማየትና ትልቅ አስተዋይ መሪ ስለመሆንዎ ለመመስከር በመብቃቴ ዕድለኛ ነኝ።

በምሰራበት ጊዜ ውስጥ ስለሌሎችም ያየሁትና የማውቀው ብዙ ነገር ስላለ የሁሉንም ሥራና ማንነት ባስፈለገ ጊዜ በዝርዝር እገልጠዋለሁ።

የግርማዊነትዎ ዋና ዓላማ ከታሪክ የወረሱትን ኃላፊነትና ከሕዝብም የተቀበሉትን አደራ በሚገባ ለመወጣትና ለተተኪው ትውልድ ፅኑ መሠረት በመጣል ታሪካዊ ቅርሳችንን አስረክበው ለማለፍ መሆኑን በሃሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባር አስረድተዋል። ይኸውም የቆሙለት ብሔራዊ ዓላማ በትክክል ግቡን እንዲመታ የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል እንዲቋቋም ከማድረግዎም ሌላ የተደከመበት ሁሉ መና ሆኖ እንዳይቀር በማሰብ ሥራው በተሟላ ሁናቴ እንዲኪያሄድ ለማድረግ ንጉሣውያን ቤተሰብና ሌሎችም ታዋቂ ግለሰቦች በሥራው ተካፋይ እንዲሆኑ ጥሪ አድርገዋል።

ግርማዊነትዎ ይህን ታሪካዊ እርማጃ የወሰዱት በግፊት አይደለም። በአገር ውስጥና በውጭም አገር ያሉ የዘውድ ደጋፊዎች በየጊዜው ያቀረቡልዎትን ጥያቄ አይተው የወደፊቱንም ሒደት ተመልክተው ላገር የሚበጅ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ነው። እንዲሁም ደግሞ የሞዓ አንበሳ ስራ እንዲቀጥል በተደጋጋሚ የሰጡት ትእዛዝ ባለመፈጸሙ ስራው እየተዳከመ በመሄዱና የሞዓ አንበሳ ቢሮ ሊዘጋ በመሆኑ ስራው ቆሞ ሕዝቡ ተስፋ ቆርጦ እንዳይበተን የተጀመረው ስራ እንዲቀጥል የሚደረግበትን መንገድ ለመቀየስና ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የቆሙለት አላማና የተለሙት አግጣጫ አስተማማኝነት ያለው መሆኑን ለሕዝብ በማረጋገጥ የዘውድ ደጋፊዎች እምነት በይበልጥ እየተጠናከረ ተሳትፎአቸው እየጨመረ እንዲሄድ ለማድረግ የሚረዳ መሆኑን በመገንዘብ ነው።

ግርማዊነትዎ የወሰዱት እርማጃና ያደረጉትም ውሳኔ ወቅታዊ ስለሆነ ሕዝቡንና በተለይም የዘውድ ደጋፊዎችን አስደስቷቸዋል። ቅር ያለው ቢኖር የግል ጥቅሙ የተነካበት መስሎ የታየው ብቻ ነው። እስካሁን ድረስ የምሰማው ከአንድ ወገን ብቻ ከሚናፈሰው የስም ማጥፋት አሉባልታ በቀር ምስጋና ነው። አብዛኛው ግርማዊነታቸው መሰረት ጥለው ቅርስ ትተው ለማለፍ የሚፈልጉ አርቆ አስተዋይ መሪ ናቸው ለካ እያለ ያደንቃል ያመሰግናል። የተደረገው ውሳኔና የተወሰደውም እርምጃ በማቃለል ውዥንብር የሚነዛው ውሳኔውንም ለማስለወጥ ደባ የሚሸርበው ከአንድ ወገን ብቻ ነው።

ይህ ሁሉ መሯሯጥ የሚደረገው ላገርና ለሕዝብ በመቆርቆር ወይም ለስራው በማሰብ ሳይሆን ነገሩን በግል ጥቅም አኳያ በማየት ብቻ መሆኑ ሁኔታውን ለሚያውቀው ሁሉ ግልጥ ነው።

ለአገርና ለሕዝብ ተቆርቁረው ለግርማዊነትዎ ክብርና ስም መጠበቅ አስበው ቢሆን ኖሮ በስምዎ የተከፈተው ቢሮ እንዲዘጋ ሥራው እንዲዳከም በማድረግ ፈንታ በሰጡት ንጉሣዊ ትዕዛዝ መሠረት ሥራው በተሟላ አኳኋን እንዲቀጥል ባደረጉ ነበር። ይህ ሁሉ የስም ማጥፋት ዘመቻ ባላስፈለገ ነበር።

ይሁን እንጂ የሚያደርጉት ሁሉ ከሚያስገምታቸውና ማንነታቸውን ከሚያሳይባቸው በቀር ሌላ የሚያስገኝላቸው ነገር የለም። ዓላማቸው ውሳኔውን ለማስለወጥ እንደሆነ የግርማዊነትዎን ሃሳብና ዓላማ ሕዝብ እንዲያውቀው ስለተደረገ ከዚህ በኋላ የሚደረገው መፈራገጥ ውርደትና ትዝብት ከሚያስከትል በቀር ሌላ ውጤት እንደማይኖረው ሊታወቅ ይገባል።

ግርማዊነትዎ ከንጉሣውያን ቤተሰብ መካከል መርጠው በስራው በመካፈል ወግና ስርዐት እንዲማሩና እንዲዘጋጁ ማድረግዎ የሚያስደስት እንጂ የሚያስወቅስ አልነበረም። ውሳኔውን በመደገፍ ፋንታ የስም ማጥፋት ዘመቻ ማካሄድ ግርማዊነትዎን መድፈር ከመሆኑም ሌላ በሕዝብና በታሪክም ፊት የሚያስጠይቅና የሚያስወቅስ አድራጎት ነው።

የስም ማጥፋት ዘመቻ የሚካሄደውና ውዥንብርም የሚነዛው ውሳኔው በግርማዊነትዎ ያልተደረገ አስመስሎ በማቅረብ ሰሚውን ወገን ለማሳሳት ነው።

በውሳኔዎ ላይ ስማቸው የተገለጠው እያንዳንዱ የንጉሣውያን ቤተሰብ አባል መርጠው የመደቡት ውሳኔውንም የሰጡት ግርማዊነትዎ መሆንዎን እኔ ተጠርቼ በተገኘሁበት ለእመቤቴ ጥያቄ አዎን በማለት ውሳኔዎን ደግመው አረጋግጠዋል። እንግዲህ ነገሩ እዚህ ላይ ሊቆም ሲገባው ከዚህ በኋላ ተሾመ ያደረገው በማስመሰል ውዥንብር መንዛት በዘውዱ አቋም ላይ አጉል ጥርጣሬ ከመፍጠሩ ለጠላትም መግቢያ በር ከመሆኑና ውዥንብር ነዥውንም ከማስገመቱ በቀር ተሾመን የሚጎዳ ነገር የለም።

ተሾመ አጭበርብሮ ወይም አታሎ አያውቅም። ተሾመ የሚሠራውን የሚያውቅ የግል ጥቅም የማይፈልግ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በልዩ ልዩ ኃላፊነት ላይ ተመድቦ ያገለገለ ማንነቱ በሕዝብ ዘንድ የታወቀ ስለሆነ በአጉል አሉባልታ የሚፈታ አይደለም። የተደረገው ሁሉ በግርማዊነትዎ ፈቃድ የሕዝብን ፍላጎት በመከተልና የልብ ትርታውን በማዳመጥ ስለሆነ የአንድ የግል ጥቅም ፈላጊ ወገን ተቃውሞ የሕዝብን ፍላጎት ሊያስቀረው አይችልም።

ዘውዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃብትና ቅርስ እንጂ የአንድ ወገን የግል ሃብት አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ግርማዊነትዎ እንደሚያውቁት በስራው ልጆችዎ ተካፋይ በመሆን ወግና ስርአት እንዲማሩ ለሃላፊነት እንዲዘጋጁ በማሳሰብ ልዕልት ስህን የምክር ቤትዎ ሰብሳቢ እንዲሆኑ ግርማዊነትዎን አስፈቅጄ ይሰሩ እንደነበር ይታወሳል በኋላ በፈቃዳቸው ለቀው ወጡ እንጂ። አሁንም ልዕልት ማርያም ሥና በሥራው እንዲካፈሉ ግርማዊነትዎ ፊት እመቤቴ ባሉበት ጠይቂአቸው ትዳሬ ይበልጥብኛል በማለት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ይህን ሁሉ ካደረኩ በኋላ ነው ከልጅ ልጆችዎና ከሌሎች ንጉሣውያን ቤተሰብ መካከል እጩዎች መርጬ ያቀረብሁት። ይህን ሁሉ የማያውቅ እንዲያውቀው ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ባዘዙኝ መሠረት ከንጉሣውያን ቤተሰብ መካከል መርጬ ከማቅረብ በቀር ሌላ ያደረኩት ነገር የለም። ራሴን ወይም ወገኖቼን አላቀረብሁም። ግርማዊነትዎማ እኔው ራሴ እንደራሴ እንድሆን ጠይቀውኝ አልነበረም ወይ? ለኔ አይገባም እንደራሴነቱ ሊሰጥ የሚገባው የንጉሣውያን ቤተሰብ አባል ለሆነ ነው በማለት ለግርማዊነትዎ አስረድቼ እንዲቀር አስደረግሁ እንጂ። ይህንንም ያደረግሁት ግርማዊነትዎ ለዚህ ታላቅ ኃላፊነት ሲመርጡኝ ሳልደሰት ቀርቼ ሳይሆን የዘውዱ ወግና ስርዓት እንዲጠበቅና ዘውዱም በሕዝብ ዘንድ መልካም ገፅታ እንዲያገኝ በማሰብ ነው።

ግርማዊነትዎም ቢሆን እኔን የመረጡት የዘውዱን ወግና ሥርዓት ሳያውቁት ቀርተው ሳይሆን ከንጉሣውያን ቤተሰብ በተለይም ከልጅ ልጆችዎ መካከል ቢመርጡ ሊደርስብዎ የሚችለውን ተፅእኖ ንትርክና ንዝንዝ በማሰብ መሆኑን ሳልገነዘበው አልቀረሁም። የሆነ ሆኖ ግርማዊነትዎ ቆራጥ ነዎትና ወደ ኋላ አላሉም። ወስነዋል ተፅእኖም ቢደረግብዎ አልተበገሩም።

ከግርማዊነትዎ ዘንድ ተጠርቼ በቀረብሁ ጊዜ እመቤቴ የተመረጡት ንጉሣውያን ቤተሰብ ተጠይቀዋል ወይ? በማለት ጠይቀውኝ የሰጠሁትን መልስ ደግሜ ላስታውስ እፈልጋለሁ። በአገራችን ወግና ሥርአት መሰረት ምታ ነጋሪት ክተት ሰራዊት ሲባል ሁሉም መሰለፍ ይኖርበታል። የንጉሥ ጥሪ ነውና ጃንሆይ ጥሪ አደረጉ እንጂ አላስገደዱም። የፈለገ ይቀበል ያልፈለገ ይተወው ግዴታ የለበትም። የሆነ ሆኖ በበኩሌ ከሁለት በቀር ሌሎቹን አነጋግሬአለሁ። ስማቸውንም ከማቅረቤ በፊት በተቻለኝ መጠን የዘውድ ደጋፊ የሆኑ ታዋቂ ግለሰቦችን አማክሬአለሁ።

በእመቤቴ በኩል ቤተሰቡ ማለትም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቤተሰብ አርባ ሲሆን አልተጠየቁም በማለት ስለቀረበው ጥያቄ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሰው እንደመሆናቸው መጠን ልጆችና የልጅ ልጆች ቢኖራቸውም በንጉሠ ነገሥትነታቸውም ቤተሰባቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ግርማዊነትዎም ቢሆን የአንድ ቤተሰብ ወይም ክላን (clan) መሪ አይደሉም። የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ንጉሠ ነገሥት ነዎት። ጉዳዩ እንደዚህ በጠባቡ የሚታይ አይደለም።

ግርማዊነትዎ ሰው አፍቃሪ እንደመሆንዎ መጠን እንኳን ቤተሰብ ይቅርና ሌላውም ሁሉ ቢሰበሰብ ደስ እንደሚልዎ የታወቀ ነው። ቤተሰቡን ለመሰብሰብ አመች ሁናቴ መፍጠር ያስፈልጋል። እስከዛሬ ቤተሰብ እንዲሰበሰብ ለማድረግ የሚያስችለው ነገር ሁሉ ስላልተደረገ ቤተሰብ ሊሰበሰብ አልቻለም። እንግዲህ ቤተሰቡ እንዲሰበሰብ ሁኔታውን ማመቻቸት እመቤቴ በእቴጌነታቸው የተጣለባቸው ኃላፊነት ሲሆን ሁኔታው እየታወቀ በዚህ በኩል እኔን መውቀስ ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም።

በጠቅላላው ስለ ሞዓ አንበሳ ስራ ሐሳብና አስተያየት ያላቸው ለግርማዊነትዎ መግለጥ እንዲችሉ በማሰብ ላለፈው ገና ቤተሰቡ እንዲሰበሰብ ለግርማዊነትዎና ለእመቤቴ አሳስቤ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃይለ ሥላሴም ተጠይቀው ስለተስማሙ በቀረበው ሐሳብ መሠረት እንዲፈጸም ተወስኖ ነበር። ነገር ግን በተወሰነው መሠረት ሳይፈጸም በመቅረቱ የታሰበው ሳይሆን ቀርቷል ከዚህም ሌላ ከቤተሰብ ውጭ በዋሽንግተን አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቀጠሮ እየተያዘላቸው ግርማዊነትዎን እጅ እንዲነሱና እንዲያውቋቸውና እንዲያውቂዎት እንዲሁም በመቤቴ በኩል ሴት ወይዘሮዎችን እየጋበዙ በማነጋገር ጥሩ ግንኙነት እንዲፈጠር ደጋግሜ ሐሳብ ማቅረቤ ይታወሳል። እንደታሰበውና እንደትፈለገው ግን ሊሆን አልቻለም። ለምን ቢባል መልሱን ለታሪክ እተወዋለሁ ካስፈለገም ወደፊት እገልጠዋለሁ።

በመሠረቱ የተመረጡት ንጉሣውያን ቤተሰብ

ወደ ገጽ 7 ይዞራል

ከገጽ 6 የዞረ

ራሳቸውን የቻሉ ስለሆነ ራሳቸውን አነጋግሬአለሁ ቢፈልጉ ከወላጆቻቸው ጋር ከሚመካከሩ በቀር እኔን የሚያገባኝ ነገር ያለ አይመስለኝም።

አረ ለመሆኑ የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ሐሳቡ ሲወጠንና አስፈላጊው ሁሉ ሲዘጋጅ ቤተሰቡ እንዲመክርበት ተደርጎ ነበር ወይ? በመጨረሻም በሂልተን ሆቴል ግርማዊነትዎ እንዲገኙ ተደርጎ ለሕዝብ በይፋ የተገለጠው ቤተሰቡ ተጠይቆ መክሮበትና ተስማምቶበት ነው ወይ? እንግዲህ በዚያን ጊዜ ያልተጠየቀው ቤተሰብ አሁን ከየት ብቅ አለ? ፍርዱን ለሕዝብና ለታሪክ እተወዋለሁ።

ግርማዊ ሆይ

ሌላው የሚናፈሰው አሉባልታ ሹመት ቀለጠ እየተባለ ነው። ከላይ እንደገለጥሁት ጃንሆይ ጥሪ አደረጉ እንጂ ሹም ሽር አላደረጉም። አሁን የተወሰደው እርማጃ ዘውዱን ወደ ነበረበት ቦታ ለመመለስ በሚኪያሄደው ሥራ ተካፋይ በመሆን ወግና ሥርዓት እንዲማሩና ለወደፊቱም ለሚጠበቅባቸው ኃላፊነት ለበለጠ ብቃት እንዲያገኙና እንዲዘጋጁ ለማድረግ ነው።

ግርማዊ ሆይ

ነገሩን ለማጠቃለል የግርማዊነትዎን ጥሪና ትእዛዝ የተቀበልሁት ለሹመት ጓጉቼ ወይም የግል ጥቅም ለማግኘት ብዬ አይደለም። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህልውና ከፍ ካለ አስጊ ሁኔታ ላይ በመድረሱ የሕዝብዎም አንድነት እየተናጋ በመሔድ ላይ በመሆኑ በዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍ ያለ ችግርና ፈተና ባጋጠመው ወቅት የግርማዊነትዎ መኖርና አለንልህ ማለት ለአገሩ ህልውና ለአንድነቱ መከበር ለሚታገለው ሕዝብ አለኝታ ይሆናል ብዬ ስለማምን፣ የጌታዬን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ውለታ ለመክፈል ስለምፈልግ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያዊነቴ ለአገር አንድነት መከበር ለሕዝብም መሰረታዊ መብቶች መጠበቅ የሚገባኝን ሁሉ የማድረግ ኃላፊነት ያለብኝ መሆኑን በመገንዘብ ነው።

ግርማዊነትዎ የሚጠበቅብዎትን አድርገዋል ታሪክ እንዳይወቅስዎ የመሸጋገሪያውን ሁኔታ አመቻችተዋል። እኔም በበኩሌ የተጣለብኝን አደራና ኃላፊነት ለመወጣት የሚጠበቅብኝን ፈጽሚያለሁ። ከእንግዲህ ወዲያ ፍርዱ የሕዝብና የታሪክ ነው።

በመጨረሻ የማወሳው የወደፊቱን ሁኔታ ነው። እንዳየሁት ሁኔታው ግርማዊነትዎ በተለሙት መሠረት ሥራው እንዲቀጥል የሚያስችል ሆኖ አላገኘሁትም። ሁኔታው ተስፋ የሚያስቆርጥ እንጅ የሚያበረታታ ሆኖ አልታየኝም። የሚታየኝ ሥራው ሲዳፈን ነው። ይህ ሊደርስ የሚችለው በግርማዊነትዎ በኩል ድክመት ኖሮ ሳይሆን በሚደረግብዎ ከፍተኛ ተፅእኖ ከበባና አፈና ነው።

ግርማዊነትዎ ቆራጥ ነዎ። በበኩልዎ የጎደለ ነገር የለም። የሚቻለዎን ሁሉ አድርገዋል። የጎደለ ቢኖር በሌላ በኩል ነው። ሐሳብዎን ተግባራዊ ለማድረግ ያላደረጉት ነገር ያልወሰዱት እርምጃ የለም። ነገር ግን ተፅእኖው ከበባውና አፈናው አስቸግሮዎታል። ይህን የምለው ያለምክንያት አይደለም። እአአ ነሃሴ 11 ቀን 1993 ዓም ግርማዊነትዎ እመቤቴ ባሉበት ልዕልት ማርያም ስና አምኃ ሥላሴ አቶ ኃይሉ ሰብስቤ ወ/ሮ ሙሉመቤት ፋሪስና እኔ ተጠርተን በተገኘንበት ስለጀኔራል ዐባይ የማኑ መሰናበት ጉዳይ የተሰጠውን ውሳኔና ትዕዛዝ አስታውሳለሁ። የተወሰነው ርክብክቡ በምክር ቤቱ በኩል በሳምንት ውስጥ እንዲፈጸም ነበር። እኔም የተሰጠኝን ትዕዛዝ ተቀብየ እጅ ነስቼ ከቢሮ ሔጄ በመሥራት ላይ እንዳለሁ በአሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ሻምበል ገድሉ ኃይሉ ከስራ የተሰናበተ ሲሆን እመቤቱ በማያገባው ጉዳይ የስንብቱን ፅሑፍ እንዲያዘጋጅ ስላዘዙት አዘጋጅቶ መጥቶ በኮምፒውተሩ ቢሮ ውስጥ ገብቶ ለመጻፍ በመሞከሩ ምክንያት የማያስፈልግ ግጭት ተፈጥሩዋል። ከዚያም አልፎ ፖሊስ ተጠርቶ እንዲወጣ በመደረጉ የቤተ መንግሥቱ ክብር ተደፍሩዋል ገበናውም ተጋልጧል። ጎረቤት ወጥቶ በማየት ጉድ ብሏል። በጠቅላላው ቤተ መንግሥቱ መሳቂያና መሳለቂያ ሆኗል።

ይህ ሁሉ የተፈጸመው ግርማዊነትዎ እኔ ባለሁበት ከሰጡት ውሳኔና ትእዛዝ ውጭ ነው። ይህ ድርጊት በግርማዊነትዎ ላይ ያለው ተፅዕኖ ከበባና አፈና የቱን ያህል ከባድ እንደሆነ ያሳያል። አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ግርማዊነትዎ ከወሰኑ በኋላ ሥርዐት ተጥሶ ክብርዎን የሚነካ ስምዎን የሚያጠፋ ድርጊት ሲፈጸም በማየቴ ወደፊት ከዚህ የባሰ ሁኔታ እንደሚደርስ መገመት አያዳግተኝም። ስለዚህ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ግርማዊነትዎን ለማገልገል የሚቻል ባለመሆኑ አገልግሎቴን ማቋረጥ ተገድጃለሁ። ይህንም ብል በኢትዮጵያዊነቴ ኃላፊነት ስለአለብኝ በውጭ ሆኜ ለዘውዱ ሕልውና ለአገር አንድነትና ለሕዝብ ደህንነት ከሚያስቡ ጋር በመሆን ትግሉን የምቀጥል መሆኔን ለግርማዊነትዎ አረጋግጣለሁ። እስካሁን ድረስ የግርማዊነትዎ መኖር አለኝታችን ነውና እግዚአብሔር በቸርነቱ እንዲጠብቅልን እፀልያለሁ።

ትሁት አገልጋይዎ

አፈንጉሥ ተሸመ ኃይለ ማርያም
8-19-93

እቴጌ መድፈሪያሽ ወርቅ ማናቸው?

ከኃይሉ በለጠ

እቴጌ ለመባል እንዴት ቻሉ? እነ እቴጌ ጣይቱ በአድዋ ጦር ግንበር ተዋግተውና ጣላትን የተቋቋሙ ያገራችን ጦር መሪ ስለነበሩ ነው።በአፍሪቃና በጠላትም በኩል የሴት ንግሥት የመባልን ታሪክ ስለ ተቀዳጁ ነው። የጠላትን ጦር ተቋቁመው ድል ከመምታታቸውም ባሻገር፣ የሃይማኖትም ጀግና ስለ ነበሩ ነው። ከዚህም በስተቀር ከጀግናው ባለቤታቸው ከዳኛው ምኒልክ ጋር በዕለተ ጊዮርጊስ ድሉን ለሰጣቸው አምላክ ምሥጋና ሲያቀርቡ እንደ ዋሉ የሃይማኖት ታሪካቸው ጭምር ስለሚመስክርላቸው ነው።

የዛሬዋ እቴጌ መድፈሪያሽ ግን፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረኃብ አለንጋ እየተገረፈ፣ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ የተወረሰውንና በስዊስ ባንክ ተቀማጭ ሆኖ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረውን ትርፍ ሁሉ በኪሳቸው አጭቀው እንደሚጫወቱበት በሞዓ አንበሳ ጋዜጣ የታተመውን እንብበን ለመገንዘብ ችለናል። ንጉሠ ነገሥቱ በሕመም እንደ ፈለጉት መንቀሳቀስ ተስኗቸው፣ ወደ ውድ አገራቸው እንኳን ለመመለስ ፈልገው በእቴጌይቱ መታገዳቸው ያደባባይ ምሥጢር ሆኗል። ከብዙ ሚሊዮን ዶላር በላይ ያለው ገንዘብ እንኳቸው በዴር ሡልጣን የሚገኘውንና ለኢየሩሳሌም ገዳም እቴጌ መነን አሠርተው ያበረከቱትን ፎቅ በወያኔው ጳጳስ በአቡነ ጳውሎስ አማካይነት ለመሸጥና በገንዘቡም ለመጠቀም በመሩዋሩዋጥ ላይ እንደሚገኙ ታውቋል። ሀብቱ ግን የኢትዮጵያ ገዳም ነው። ከእቴጌ መነን በፊት እቴጌ ጣይቱ ተመሳሳይ ፎቅ አሠርተው ኢየሩሳሌም ለሚገኘው "የዴር ሡልጣን" ገዳም ማበርከታቸው የታሪክ ማስረጃ ነው። ሆኖም የንጉሠ ነገሥቱ ድርሻ የሚሆነውን የእቴጌ መነን ፎቅ በወያኔው ሠላይ በጳጳሱ አማካይነት ለመሸጥ በጥድፊያ ላይ እንደሚገኙ ስናረጋግጥ፣ በብስጭት እየተቃጠልን፣ ራሳችንን በራሳችን እያስታገሥን እንገኛለን።

ስለዚህም የእቴጌይቱ ጉዳይ አንድ መሥመር ካልያዘና በረኃብ አለንጋ የሚገረፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ መፍትሔ ካላገኘ፣ ባስቸኳይ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር አገሪቱን ለማዳን መተባበር ይኖርብናል። የሃይማኖት ሰዎችና አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአንድነት ሠላማዊ ሠልፍ እንዲያደርጉና ታፍነው የተያዙትን ንጉሠ ነገሥት ከዕሥራት ነፃ አስወጥተን አገራችንንና ዘውዱን ከዚህ ታላቅ አደጋ እንድናድን ኃላፊነት አለብን። ከባዱንም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወረሰውን ሀብት ከመንጋጋዋ አላቅቀን ለረኃብተኛው ኢትዮጵያዊ እንድናውለው የሞዓ አንበሳ አባላት በሙሉ የሕዝቡን ትብብር አጥብቀው ይጠይቃሉ።

በዙፋን ምክር ቤት ፀድቆ በንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ጽሕፈት ቤት ሹም በጄኔራል ዓባይ የማኑ አማካይነት ተርቦላቸው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አምኃ ሥላሴ ሹመቱ ሲሰጡ።

ሐምሌ 2/ ቀን 1985 ዓም

ለአቶ ዳምጤ አለማሽኝ
የሞዓ አንበሳ ጋዜጣ አዘጋጅ

በሐምሌው የሞዓ አንበሳ ጋዜጣ እትማችሁ ላይ ሰፋ ያሉ ዝርዝሮች በማብራራት ያቀረባችሁትን አንብበናል። ይኽም የሞዓ አንበሳ በጣም የሚያስመሰግናችሁ በመሆኑና በኢትዮጵያውያን ወገናችሁ በኩል የቆማችሁ መሆኑን ስለሚያስረዳ በታላቅ አክብሮት ልንገልፅ እንወዳለን።

ንጉሠ ነገሥቱ በሰጡት ውሳኔ ሥራውን ለመምራት እቴጌይቱ እንቅፋት መሆናቸውን ተረዳን። በሞዓ አንበሳ ሒደት ላይ ደባ መፈፀማቸውን የዘውድ ምክር ቤቱ ባስተላለፈው ውሳኔ ተብራርቷል።

በዚሁ መሠረት ንጉሠ ነገሥቱ እስከ ወዲያኛው በዘውድ ምክር ቤቱ አመራርና በማንኛውም ጉዳይ በስማችን በምንሠራው ሁሉ እንዳትገባ ብለው ያስተላለፉት ንጉሣዊ ውሳኔ ከፍተኛ ማስረጃ መሆኑን በጋዜጣችሁ ዓምድ ገልጸችሁታል።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ አምኃ ሥላሴ በሰጡት ትእዛዝ መሠረት ልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ ከዙፋን ምክር ቤቱና ከሞዓ አንበሳ አባሎች ጋር በኃላፊነት እንዲመሩ የተረበላቸውን ጥያቄ መቀብላቸውን አረጋገጡ።

አቀራረባችሁን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንዲረዳው በማድረጋችሁ፣ የሕዝቡ ድጋፍ እንደማይለያችሁ ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን።

በንጉሠ ነገሥቱ አዋጅና ተደጋግሞም በተገለፀው ሁሉ፣ ልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ ምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ሆነው እንዲመሩ ሥልጣኑን ተረክበዋል።

ስለዚህም በአዲስ አበባ ዋና ከተማና፣ በወሎ፣ በጐንደር፣ በጐጃም፣ በሸዋና በሌሎቹም ክፍላተ ሀገር የምንገኝ የሞዓ አንበሳ ዓላማ ተከታዮችና አባሎች በሙሉ፣ ልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ ምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ሆነው ሥራውን ባስቸኳይ እንዲቀጥሉና እንዲመሩ እንጠይቃለን።

ይህንንም ውሳኔ ያስተላለፍነው ታላቅ ስብሰባ አድርገን ውሳኔውን ባፀደቅነው ዕለት ሲሆን፣ ይኸንኑም ውሳኔ ለሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል ምሥራቅ አፍሪቃ ለሚገኙት ኃላፊዎች አስተላልፈናል። ይቅናችሁ ----

ቀጥሉ---

ሹመት

መጋቢት 27 ቀን 1980 ዓም ንጉሠ ነገሥቱ ሾመዋቸው ከነበሩትና ጋዜጣው በንግሥቲቱ አደናቃፊነት ተዘግቶ ስለ ነበረ በሞዓ አንበሳ ጋዜጣ ስማቸው ሳይዘረዘር ከቆዩት ባለውለታዎች ውስጥ የሚከተሉት ክቡራን የተሾሙ ሲሆን የቀሩትንም ሌሎች ክቡራን ሹማምንቶች ወደፊት በተከታታይ እንገልጻለን።

ሡልጣን አሊ ሚራህ ሐንፍሬ - ንጉሥ
ደጃዝማች ብርሃነ መስቀል ደስታ ራስ
ቢትወደድ አዳነ መኰንን
- ቢትወደድ ራስ
ደጃዝማች ፀሐዩ ዕንቁ ሥላሴ - ቢትወደድ ራስ
ልጅ መርዕድ ብሩ - ራስ
ልጅ ታደሰ ብሩ - ራስ
ደጃዝማች ከበደ ብዙነሽ - ራስ
ፊታውራሪ በላይ ዘለለው - ቢትወደድ ራስ
ግራዝማች ጉግሳ አንባው - ራስ
ቀኛዝማች ስሜነህ (ሲዋጉ የሞቱ) - ቢትወደድ
አቶ ዘነበ ኃይሌ - ቢትወደድ
አቶ ተክሌ ሮሮ - ቢትወደድ
ዶክተር ጌታቸው መካሻ - ቢትወደድ
ቀኛዝማች ስሜነህ ሲዋጉ የሞቱ - ቢትወደድ
ቀዝማች ሐምፍሬ አሊ ሚራህ - ቢትወደድ
ሻለቃ አጣናው ዋሴ ቢትወደድ (ከደርግና
ከወያኔ ጋር እስከ አሁን የሚዋጋ)
ልጅ አድማሱ ጀንበሬ - ቢትወደድ
ቀኛዝማች ታደሰ ዕንቆ ሥላሴ - ደጃዝማች
ባላምባራስ በዛብህ አደመ - ደጃዝማች
ሻለቃ በላይ አሊጋዝ - ደጃዝማች
ቀኛዝማች ታፈራ እጅጉ - ደጃዝማች
ግራዝማች አበራ በላይ - ደጃዝማች
ልጅ መለሰ እየለ - ደጃዝማች
ልጅ በቀለ ዘውዴ - ደጃዝማች
ግራዝማች ሹመት ስላምሳ - ደጃዝማች
ግራዝማች መንገሻ እየለ - ደጃዝማች
ባላምባራስ ሞገስ ድሌ - ደጃዝማች
ሻለቃ ደሴ የማነ - ደጃዝማች
ፊታውራሪ ዳኘነቱ ሻረው - ደጃዝማች
ሐጂ ጋአስ አዶዩ - ደጃዝማች
ሻለቃ ወሌ ታደሰ - ደጃዝማች
ፊታውራሪ ተስፋዬ እስናቀ - ደጃዝማች
ሻለቃ ደሴ ስንቄ ደጃዝማች
ፊታውራሪ መኰንን መልዓኩ ደጃዝማች
አፈራ አዳነ ደጃዝማች
በላይ ብዙነህ - ደጃዝማች
ፊታውራሪ አዲሱ መኰንን - ደጃዝማች
ፊታውራሪ የሺ ወንድም ናደው - ደጃዝማች
ኃይሉ ሺበሺ - ደጃዝማች
አብርሃም መሸሻ የሞቱ - ደጃዝማች
ፊታውራሪ አበራ ጣሰው የሞቱ - ደጃዝማች
ሻለቃ ገላዬ ልየው - ደጃዝማች
ሻለቃ አስራደ በየነ - ደጃዝማች
ሻለቃ ዋቅሹም ነወጠ - ደጃዝማች

መቶ አለቃ ዓለማየሁ ወረኛ - ደጃዝማች
ቀኛዝማች አድማሱ በላይ - ደጃዝማች
ፊታውራሪ አሰፋ ታረቀኝ - ደጃዝማች
ፊታውራሪ ፍስኃ እንግዳ - ደጃዝማች
ፊታውራሪ መኩሪያ ዘገየ - ደጃዝማች
ፊታውራሪ ኃይሌ ጉበና - ደጃዝማች
ልጅ አበታ ሙላት - ደጃዝማች
አቶ ሰይፉ አስፋው - ደጃዝማች
ኰሎኔል ታረቀኝ ገብረ መስቀል - ደጃዝማች
ልጅ አግባው ውብነህ -ደጃዝማች
ቀኛዝማች ጣሂሮ ሐመዶ - ደጃዝማች
ሻለቃ ወንዴ ታየ - ደጃዝማች
ልጅ ጉግሳ ከበደ - ደጃዝማች
ባላባራስ ዘርፉ ዳምጤ - ደጃማች...
አቶ አማረ ጉግሳ - ደጃዝማች
አቶ ጌትነት አለበል - ልጅ
አቶ ጥላሁን አማረ - ፊታውራሪ
አቶ ካሤ ዋዩ - ፊራታውራሪ
አቶ ቦጋላ ታክለ ማርያም - ፊታውራሪ
ሻለቃ ዱባለ ምንይሉ - ፊታውራሪ
አቶ ከበደ ምሕረቴ- ፊታውራሪ
ሻምበል ይፋት አስገድ - ፊታውራሪ
አያልነህ መስፍን - ፊታውራሪ
ሙኰንን ደሳለኝ (ፊታውራሪ)

አህመድ መኰንን - ፊታውራሪ
ሻምበል አድማሱ ነወጠ - ፊታውራሪ
ሻምበል መሐመድ ሠይድ - ፊታውራሪ
ባላምባራስ ኪዴ ጉላ - ፊታውራሪ
በትሩ እጅጉ - ፊታውራሪ
ስማቸው በላይ - ፊታውራሪ
ብሩ መኰንን - ቀኛዝማች
ሐጂ ኢብራሂም ውብነህ - ቀኛዝማች
ሐጂ መሐመድ ሐቢብ - ቀኛዝማች

ይቀጥላል.....

ማሣሠቢያ

ከሐምሌው እትማችን ላይ አንብባችሁ አስተያየታችሁን በሰፊው ስለ ጻፋችሁልን በጣም እናመሰግናለን። በጻፋችሁልን መሠረት መልሱን ለመጻፍ ከ67 በላይ ደብዳቤዎች ስለ ደረሱን ለያንዳንዱ ደብዳቤ መልስ ለመስጠት ተቸግረናል። ባሁኑ ጊዜ ያተኰርንባቸውና ለኅዝቡ በቅድሚያ የሚገለጹ ጉዳዮች ስላሉን በየጊዜው በተከታታይ የናንተንም ደብዳቤዎች ጭምር እናስታውቃለን።

በጻፋችሁልን ደብዳቤዎች ላይ እንደተመለከትነው አብዛኞቹ አንድ ዓይነት ጥያቄዎች ያዘሉ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ በዛ ያሉ ጥያቄዎች በንጉሠ ነገሥቱ አዋጅ መሠረት ለመሥራት ንጉሠ ነገሥቱ የተቸገሩበትን ባለፈው እትማችን አሣውቀናል።እቴጌዋ ንጉሠ ነገሥቱን ማስቸገራቸውንና ገንዘባቸውን ይዘው የኢትዮጵያን ሕዝብ መበደላቸውን የኢትዮጵያንም ሃብት ዘርፈው ለምን አልተጠየቁበትም ለተባለው እኛ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስፈላጊውን ሁሉ አስታውቀናል። ከዚህ በኋላ ለመጠየቅ ሥልጣን ያላቸው፣

1ኛ. የዙፋን ምክር ቤት
2ኛ. የንጉሠ ነገሥቱ ጽ/ቤት
3ኛ. የሞዓ አንበሳ ሐላፊዎች ናቸው።

ከዚህም ሌላ ከልዕልት እጅጋየሁ አምኃ ሥላሴ የተወለዱት ልጆች የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል።

ኦዲተር ሊያጣራው ነው።

ከሐምሌው እትም የቀጠለ

እቴጌ መድፈሪያሽ ወርቅ "ኦዲተር" የሚባለውን ቃል ለመስማት አይፈልጉም። ገንዘብ የለም እያሉ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት መፈንጠዝ ተያያዘውታል። ንጉሠ ነገሥቱ ደሞ ገንዘብ አለን ይሠራበት ይላሉ። ይኸንኑ ትዕዛዝ ለማደናቀፍ ዘዴ መፍጠር ግድ ሆኖባቸዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ የንጉሠ ነገሥቱን የዘውድ ምክር ቤት መመሪያ አደናቀፉ። ቀጥሎም የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ጽሕፈት ቤትና የበላይ ኃላፊ ሥራውን እንዲያቆም ተደረገ። ከዚህም በኋላ የሞዓ አንበሳ ምክር ቤት ተዘጋ። ይኸም ሠራተኞችን ያቀፈ ድርጅት በሙሉ እንዲዘጋ ሲደረግ በአዲስ አበባ የዙፋን ምክር ቤት ተጠሪ የነበሩት ዶክተር ኃይለ ጊዮርጊስ የሞዓ አንበሳም ምክር ቤት የበላይ ወሳኝ ሆነው ይሠሩ ስለ ነበረ እንዳይሠሩ ሆኑ፥ ሥራው በዚህ ዓይነት ሲናጋ በሥራው ላይ ያልነበሩትን እነ አበራ ሞልቶትን በማሳሳት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ "ፀሐፊው ታገዱ" የሚል ሐተታ አሳተሙ። ስለዚህም ጠቅላላውን መሥሪያ ቤት የዘጉት "ኦዲተር" ሲታዘዝ ነው።

አቶ ሠይፉ ዘውዴ የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ እንደራሴ ሆኖ የተሾመ ሲሆን፣ ልዕልት ማርያም ሥና አምኃ ሥላሴን ያገባ የንጉሠ ነገሥቱ አማች ነው። ንጉሠ ነገሥቱ ሚያዝያ 18 ቀን 1985 በሰጡት ትዕዛዝ "በጃንሆይ ስም የተሠራውን ሁሉ ወጪና ገቢው እንደራሴ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ በኦዲተር ተጣርቶ እንዲቀርብ አዘዙ።" ንግሥቲቱ በበኩላቸው "የነበረንን ዘጠኝ መቶ ሺህ ዶላር አምጥቼ ወጪ ሆኖ አልቋል፣ ምንም የለንም፣ ያለ ቢኖር ለጌቶቹ መጠባበቂያ ብቻ የሚሆን ነው ስላሉ፣" ዶክተር ጌታቸው "እመቤቴ ለሥራው እንኳንስ ዘጠኝ መቶ ሺህ ይቅርና ከዚያም መለስ ያለ ገንዘብ የወጣ አይመስለንም፣ ስለዚህ ሂሳቡ በኦድተር ቢጣራ ቅር ይልዎታል?" ብለው ቢጠይቋቸው ደስ ይለኛል ብለው ፈቅደዋል። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም ከዚያም በፊት የሰጡትን ትዕዛዝ በማስታወስ ሁሉም በኦዲተር ተጣርቶ እንዲቀርብ አዘዋል።

በዚሁ መሠረት ሥራውን ለመቀጠል የተዘጋጀን መሆኑን ለአንባቢያን እየገለጽን፣ የምክር ቤቱ ያስተላለፈውንና ንጉሠ ነገሥቱ የተቀበሉትን እንደሚከተለው እናቀርባለን።

ሚያዝያ 18 ቀን 1985 ዓም

በሥራው ስለተወሰነ ባጀት ጉዳይ በየጊዜው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ገንዘብ ስላለን ሥራው እንዲቀጥል በማለት የማያዳግም ውሳኔና ትእዛዝ ሰጥተዋል። እቴጌ ግን የነበረን ገንዘብ በየጊዜው ወጭ ሆኖ ስላለቀ አሁን ገንዘብ የለም በማለታቸው አፈ ንጉሥ ተሾመ ግርማዊነታቸው ደጋግመው የሰጡት ትዕዛዝ የንጉሥ ቃል ስለማይታጠፍ መፈጸም አለበት፣ ይሁን እንጂ በግርማዊት በኩል ገንዘብ ሁሉ ወጭ ሆኖ አልቋል ስለተባለ እስካሁን ድረስ በጃንሆይ ሥም የተሠራው ሁሉ ወጭና ገቢው እንደራሴ ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ በኦዲተር ተጣርቶ እንዲቀርብ አሳስበው ታኅሣስ 30/85 ዓም በዚሁ መሠረት እንዲፈጸም ግርማዊነታቸው ትዕዛዝ ሰጥተዋል።

ከዚያም ወዲህ ሚያዝያ 11/85 ዓም ይኸው ጉዳይ እንደገና ተነስቶ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ገንዘብ አለን ሲሉ ግርማዊት በበኩላቸው የነበረንን ዘጠኝ መቶ ሺህ ዶላር አምጥቼ ወጭ ሆኖ አልቋል ምንም የለንም ያለ ቢኖር ለቤት ወጭና ለጌቶቹ መጠባበቂያ ብቻ የሚሆን ነው ስላሉ ዶክተር ጌታቸው እመቤቴ ለሥራው እንኳንስ ዘጠኝ መቶ ሺህ ይቅርና ከዚያም መለስ ያለ ገንዘብ የወጣ አይመስለንም ስለዚህ ሂሳቡ በኦዲተር ቢጣራ ቅር ይልዎታል? ብለው ቢጠይቋቸው ደስ ይለኛል ብለው ፈቅደዋል። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም ከዚያም በፊት የሰጡትን ትዕዛዝ በማስታወስ ሁሉም በኦዲተር ተጣርቶ እንዲቀርብ አዘዋል።

ምክር ቤቱ በዚህ በሰፊው ተነጋግሮበት ይህ በእቴጌ የተጠቀሰው ገንዘብ ለሥራው ጉዳይ ወጭ መሆኑን እስካሁን አጥጋቢ ማስረጃ አላገኘም፣ ለዚህ ሁሉ ትክክለኛው ሊታወቅ የሚችለው በኦዲተር ሂሳቡ ሲመረመር ስለሆነ አስፈላጊው ወጭ ተደርጐ ኦዲተር ባአስቸኳይ እንዲቀጠር በማለት ወስነናል።

የጅቡቲው ደብዳቤ (ስለ ልዕልት ማርያም ሥና)

ከሐምሌው እትማችን የቀጠለው

ልዕልት ማርያም ስና ተሰጥቷቸው በነበረው ታላቅ የክብር ኃላፊነት የዘውድ ምክር ቤቱን ሰብሳቢነት፣ በግል ፈቃዳቸው ሥራውን ለቀው መሄዳቸውን ባለፈው እትማችን መግለፃችን ይታወሳል።

ልዕልት ማርያም ስና የዘውድ ምክር ቤቱን ሕግና መመሪያ በመጣስ ከእናታቸው ጋር ተማክረው የአባታቸውን ትዕዛዝ ለሁለተኛ ጊዜ ጥሰው የራሳቸውን መዋቅር ዘርግተዋል። አያታቸው አፄ ኃይለ ሥላሴ የተናገሩትን ባለመገንዘብና "ከትልቅ ተወልጃለሁ ማለት በቂ አይደለም እራስን ለትልቅ ሙያ መውለድ እንጂ" ያሉትን ታላቅ ምሳሌ ዘንግተው በስም ሊኮሩ ሞክረዋል። ጅቡቲ ለሚገኘው የዘውድ ምክር ቤት ሃላፊዎች ሕዳር 9 ቀን 1986 ዓም ለጻፉት ደብዳቤ የተሰጣቸውን መልስ በታሪክ መዝግበን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው አድርገናል። ደብዳቤውም እንደሚከተለው ነው።

ወደ ገጽ 9 ይዞራል

ከገጽ 8 የዞረ

ጅቡቲ ህዳር 9/1986 ዓም

ለልዕልት ማርያም ሥና እምኃ ሥላሴ

ለልዕልትነትዎ የሚገባ የአክብሮት ሠላምታችንን እናቀርባለን፣ ህዳር 3 ቀን 1986 ዓም በቴሌክስ ያስተላለፉልንን ደብዳቤ ደርሶን ተመልክተነዋል።

ይሔውም ለልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴና ለአፈንጉሥ ተሾመ ኃይለ ማርያም መግለጫ በማስተላለፋችን፣ ጀኔራል አባይ የማኑን ስለማወቃችንም ጭምር ባጠቃላይ በጽሑፉ ቅሬታ እንዳደረብዎ በመግለጽ ማስገንዘቢያ ብለው ጽፈውልናል።

እዚህ ላይ ልዕልትነትዎ በመግለጫችን ላይ ቅር የተሰኙበት ምኑ ላይ እንደሆነ ካለመግለጽዎም በላይ ምናልባት የጻፍነው የአቅዋም መግለጫ ለዘውድ ምክር ቤቱ እንጂ ከላይ ለተጠቀሱት የዘውድ ምክር ቤቱ ከፍተኛ ተጠሪዎች ለግላቸው ያለመሆኑን ያልተገነዘቡና እንዲያውም መግለጫውን በብሩህ ልቦና ያልተመለከቱት መሆንዎን ልንረዳ ችለናል፣ ነገር ግን ልዕልትነትዎ ንጉው ነገሥት አባትዎን አፄ እምኃ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴን ነው የሚቃወሙት ወይንስ ማንን? እኛ እንግዲህ አቅዋም መግለጫችን ተወዳጅ አባትዎ በታሪክ የወረሱትን የኢትዮጲያን ንጉሠ ነገሥት ዘውዳቸው እንዲከበር እንጂ ከዚህ ውጭ ስላይደል በዚህ ላይ ያለዎትን አቅዋምዎን ቢገልጡልን የተሻለ ነው።

ጀኔራል አባይ የማኑን እናውቃቸዋለን የምናውቃቸውም ለንጉሠ ነግሥቱ ዘውድ ተመልሶ መቋቋም ጥረት ያደረጉና ምናልባት ሌሎቻችሁ የዘውዱን ስም መጠቀሚያ በማድረግ በድሎት ስደት በምትገኙበት ጊዜና፣ በሌላ በኩል ደግሞ በጊዜው በነበረው መንግሥት ፕሮፓጋንዳ ዘውድን መደገፍ እንደትልቅ ነውርና ወንጀል ይታይ በነበረበት ጊዜ ለሕይወታቸው ሣያስቡና ሳይሳሱ፣ ከአገር ወደ አገር እየተባረሩ በነበሩበት ወቅት ጥቂት አገርና ንጉሠ ነገሥት ወዳጆችን በማግባባት በማሣመን አስተባብረው የዘውድ መንግሥት እንደገና ተመልሶ እንዲቋቋም በማድረግ ረገድ መጣራቸው ከናንተም የተሠወረ አይደለም።

በመሆኑም በናንተ በንጉሣውያን ቤተሰብ ሊመሰገኑና ሊከበሩ የሚገባቸው እንጂ፣ ትናንት አቶ፣ ዛሬ ደግሞ ጭራሹኑ ከልዕልትነትዎ በማይጠበቅ አባባል አቶነቱም ቀርቶባቸው ንጉሠ ነገሥቱ አባትዎ የሰጡዋቸውን ጀኔራልነት በመተው አባይ የማኑ በሚል መጻፉ እጅግ ቅር የሚያሰኝ ነው።

በመሠረቱ እኛ እምነታችን ለጥሩና ፍጹም በሆነ ዲሞክራሲ አሠራር ስለሆነ፣ የሠጠነው የአቅዋም መግለጫም የዘውድ ምክር ቤቱ ያዋቀራቸውን መመሪያዎችና ውሳኔዎችን በመከተልና በማመንም ጭምር ነው፣ ስለዚህ መግለጫውን አስመልክተው "የርሱ ትንፋሽ መሆኑን ባናጣውም" ላሉት፣ እኛ ቀደም ሲል በስደት የሚገኘውን መንግሥት መሠረት የጣልንና ብዙ መመራመር፣ መገመት፣ አርቆ ማስተዋልን የያዝነው ዕድሜ የማይነፍገን ሆኖ ሣለ ከእርስዎ የንጉሠ ነገሥቱ ልጅ ከሆኑት ከልዕልትነትዎ የተሰነዘረብን አባባል የማይጠበቅ ነው። በበኩላችን አሁንም ሆነ ለወደፊት ለኢትዮጵያ ታሪክ አለኝታ ለሆነው ፍጹም ዲሞክራሲ ላለው ለዘውድ መግንሥት ትግላችንን የማናቋርጥ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እየገለጽን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ በመካሄድ ላይ ያለው የቤተ መንግሥት መከፋፈልና ስርአተ አልባነት እዚያው ሊስተካከልና በጨዋዎች ሊመከርበት ሲገባው ወደ አደባባይ ወጥቶ በመዛመት ላይ ስላለ አሣፋሪው ተግባር እንዲገታ አጥብቀን እንጠይቃለን።

እጅግ የሚያሳዝነውም፣ በተለይ ባሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ ንጉሠ ነገሥታችን መቼ ይመጣሉ? እያለ በተስፋና በታላቅ ጉጉት ነገ ተነገወዲያ እያለ በናፍቆት ሲጠባበቅ ሳለ በእናንተ በዋናዎቹ አካል አለመግባባትና መናቆር ጊዜ መፍጀቱ ብሎም ማባከኑ እስከወዲያኛው ከማሳዘኑም ሌላ የታሪክም ተወቃሽ እንደምትሆኑ አትጠራጠሩ።

ጥቁሩ የአፍሪቃ አሜሪካዊ ዶክተር ሪቻርድ ሮቢርት በሰሜን አሜሪካ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እምኃ ሥላሴ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው የሚገቡበትን የዕርዳታ ገንዘብ ሲያዘጋጁ።

በመጨረሻም ልዕልትነትዎ እንዲያውቁልን የምንሻው፣ ይህንን መልስ ልንሠጥዎ የበቃነው የንጉሠ ነገሥቱ ልጅ በመሆንዎ ለንጉሠ ነገሥቱ አባትዎ ክብር ስንል እንጂ በመሠረቱ አጻጻፍዎ ስርዓትን የተከተለ ካለመሆኑም ሌላ በዘውድ ምክር ቤት ውስጥ የኛ ቀጥታ ግንኙነት ከዋናው አካል ጋር እንጂ ከኮሚቴ ጋር ባለመሆኑ ነው።

ከማክበር ከሰላምታ ጋር

አምድ 10 ቅ. ጽ/ቤት

ጅቡቲ

ግልባጭ፣

ለልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ
የዘውድ ምክር ቤት ሰብሳቢ
ፕሬዚዳንት
ለአፈንጉሥ ተሾመ ኃይለ ማርያም
የዘውድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት

በደርግ ላይ የታደመውና በኛም ላይ የተፈፀመው

ምሥጢር

=======

ኢሳይያስ አፈወርቅና መለስ ዜናዊ ደርግን ለመጣልና በኢትዮጵያም ላይ አቅደውት የነበረው አድማ እንደሚከተለው ሲሆን እኛን ለማጥፋት ስምምነት ያደረጉትም እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ1989 ነበር። ይኸንኑ ጠንቅ "ኬጂቢ" የተባለው የመስኮብ የስለላ ድርጅት ከሱዳን ዋና ከተማ ከካርቱም የስምምነቱን ዜና በአየር ጠልፎ ሊወስደው ቻለ። "ሞሣድ" ደግሞ ይኸንኑ ቃል በአየር "ከለንደን" ጠልፎ ካወጣ በኋላ፣ ምሥጢሩ አሁን የተገኘውና ወደ አማርኛ የተተረጐመው ከዋስር ሲራጅ ከናይሮቢ ኬንያ ሲሆን ቃላቱም የሚከተሉት ነበሩ።

የጋራ አቋም ወይም ቃል ኪዳን

====================

ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት የወያኔ ሐርነት መሪ አቶ መለስ ዜናዊ የዛሬ ኢሕአዴግ መሪና የኤርትራ ሕዝባዊ ሐርነት መሪ አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ ከሁለት የተውጣጣ ቡድን በሱዳን ዋና ከተማ ካርቱም ውስጥ ስበሰባ አድርገው ነበር። በኢሳይያስ አፈወርቂ ሰብሳቢነት ሁለት ቀን ተከቱል በፈጀ ስብሰባቸው የጋራ አቋም መግለጫ አስተላልፈዋል። በመግለጫውም መሠረት ዋና ዋናዎቹ አሥር ነጥቦች፣

1. በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራ ቡድን የወያኔ ትግራይ ሐርነት መባሉ ቀርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ግንባር ታጋይን በጥራት በመመልመል ደርግን መጣል ወይም ከሥልጣን መገልበጥ፣

2. ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ደርግ ያስታጠቃቸውን በደርግ ዘመነ መንግሥት የታጠቁትን ትጥቅ በማስፈታት ከፍተኛ ምሁራንና የፓርቲ አባል የሆኑትን በማጥላላት ለሁለት ወር የቀረውን ሕዝብ ማረጋጋት፣

3. ከሁለት ወር በኋላ በጣም ጥንቃቄ በተሞላበት አንድ ብሔራዊ ኮንፍረንስ የሁሉም ብሔረሰብ የሚካፈልበት የሽግግሩ መንግሥት በምንም ዓይነት ከኢሕአዴግ አቋም ውጭ እንዳይሆን መጠንቀቅ፣

4. የኢትዮጵያ ሕዝብ ከችግሩ አንፃር የኢሕአዴግን መንግሥት የሚቀበል ቢሆንም በኤርትራ ጉዳይ ላይ ጭቅጭቅ ማንሳታቸውና የኤርትራን መገንጠል የማይቀበሉ መሆናቸው ግልፅ ስለሆነ፣ የኤርትራ ጉዳይ በኢሕአዴግ አቋም ውስጥ ማካተትና ለሕዝብ በመግለጽ የሕዝቡን ዕምነትና ጥርጣሬ መለወጥ።

5. የኤርትራን ነፃ መንግሥት አዋጅ ለሁለት ዓመት ተኩል ማቆየትና እስከዚያውም በውስጥ ጊዜያዊ መንግሥት ማስተዳደርና በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የኤርትራን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ በመተባበር ማሳደግ፣ የመከላከያ ኃይሏንም በብዛትና በጥራት ማሳደግ፣

6. በአንፃሩ በመለስ ዜናዊ በኩል ያለው መንግሥት ለውስጥ ተቀናቃኞች መከላከያ ብቻ በመጠን የመከላከያ በጀት በዓመት 0.03% በማድረግ የመከላከያ ኃይሏን በጣም ዝቅ ማድረግ።

7. የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ትብብር ፖሊሲ በሚል አማካኝነት በመተባበር ከኢትዮጵያ ይልቅ የኤርትራን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ።

8. ከሁለት ዓመት ተኩል በኋላ ኤርትራ በኢኮኖሚም ሆነ በመከላከያ የበላይነት ስለምትቀዳጅ ነፃነቷን አረጋግጣ የታወቀ ነፃ መንግሥት ከማወጅ የሚያግዳት ምንም ነገር የለም።

9. ይህንን ጠንካራ አቋማችንን የሚያኮላሽ ሌላ ኃይል ከመጣ በአስቸኳይ ተገናኝተን ሌላ የአቋም ለውጥ ወይም የአቋም ማሻሻያ ማድረግ አለብን።

10. የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ/ፖሊሲ ለሕዝብ ሳይገለጥና ሳይደበቅ ለከፍተኛ ፖለቲካ ሲስተም/በመረጃ መጠበቅ አለበት ሲል "ዋሲር ሲራጅ" ከናይሮቢ ባስተላለፈው ለመረዳት ችለናል። ሆኖም የኢሣይያስ አፈወርቂና የመለስ ዜናዊ የአሻንጉሊት መንግሥት ኢትዮጵያን ይገዟታል ማለት ዘበት ነው።

"ቢወልደኝ ንጉሥ"

"ብወልደው ንጉሥ" (ደጃዝማች ከበደ ተሰማ)

ይህንን ቃል ተናግረውት የነበረው ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ነበሩ። እንደ አነጋገራቸው ደጃዝማች ከበደ ተሰማን ከሥራ ቤት ገረዳቸው የወለዷቸው አፄ ምኒልክ መሆናቸውን ሲገልጹ ነበር። በሁለተኛው ደረጃ ደግሞ የደርግ ሊቀ መንበር የነበረው መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን "ጦጢት" ትባል ከነበረው የንግሥት ዘውዲቱ ደንገ ጡር፤ ሴት ልጅ ወልደው ስለ ነበረና ያቺም ሴት ልጅ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ስለ ወለደች "መንግሥቱ ኃይለ ማርያም" የነገሠ መስሏቸው "ብወልደው ንጉሥ" ብለውታል።

ተንኰለኛው ደጃዝማች ከበደ ተሰማ የንግሥት ዘውዲቱ እጅ አስታጣቢ እንደ ነበሩ ታሪክ ይመሰክራል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዚያን ጊዜ አልጋ ወራሽ ነበሩ። በዘመኑ የነበሩ መኳንንቶች ንግሥት ዘውዲቱን በመርዝ ያስገደሉ ደጃዝሞች ከበደ ተሰማ መሆናቸውን ሲገልጹ፣ በዚያን ጊዜ ተገጥሞ የነበረው ቅኔ ያስረዳል። የሆስፒታሉም ሐኪሞች ከስዊድን አገር የተቀጠሩ ነበሩ። የሆስፒታሉ ዋና መሪ ዶክተር "ሐነር" ይባል ነበርና ንግሥት ዘውዲቱ በመርዝ የሞቱ መሆናቸውንም ለመግለጽ የተገጠመው ቅኔ እንደሚከተለው ነበር።

"አይወዱም ነበረ፣ ድመት በቤታቸው

ወደ ገጽ 10 ይዞራል

ከገጽ 9 የዞረ

ደግሞም ንግሥቲቱን "ሐነር" ገደላቸው" የተባለው በመርዝ መሞታቸውን ለማስረዳት የተገጠመ ነበር።

የደጃዝማች ከበደ ተሰማ ተንኰል በዚህ ብቻ አላበቃም ። ደርግ ሥልጣኑን በኢትዮጵያ ላይ እንዲዘረጋ ያደረጉት ደጃዝማች ከበደ ተሰማ መሆናቸውን ታሪክ እንከታተል። ደጃዝማች ከበደ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጨረሻ ዘመን የግቢ ሚኒስትር ነበሩ። የደርግ ሊቀ መንበር የነበረው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የልጅ ልጃቸው ነው። ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የቀዱትን የዕለት ወሬ በሙሉ ወዲያው ለመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ያቀብሉታል። በዚሁ ዓይነት እያንዳንዱ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባለሥልጣን ከየመሥሪያ ቤቱ፣ ከግል ቤቱና በየመንገዱ ሳይቀር እየተያዘ እንዲታሠር አደረጉ። በመጨረሻውም የልፍኝ አስከልካዮቻቸው ከጐናቸው ተይዘው ታሠሩ።

ንጉሠ ነገሥቱም ብቻቸውን መቅረታቸው ሲረጋገጥ እጃቸውን እንዲሰጡና እንዲታሰሩ ታዘዙ። በዚህም ጊዜ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ከዙፋኑ ላይ ወጥቶ ቂጥ አለ። ደጃዝማች ከበደ ተሰማም "ብወልድ ንጉሥ" ያሉት በዚሁ ወቅት ነበር።

ካሣ ከበደም "የዘሬን ብትው ያንዘርዝረኝ" እንደ ተባለው ሁሉ፣ ያባቱን ጋሻ በማንሣት በአሁኑ ጊዜ በአፄ አምኃ ሥላሴ ቤተ መንግሥት የጭኑ በሆነችው የንግሥቲቱ ያክስትና ያጐት ልጅ አማካይነት ጆሮ ለጆሮ ማጣባቱን እያጐላው ሔዷል። ምኞቱም እንደ አባቱ ሥልጣን ለመቀማትና ለማስቀማት መሆኑ ያደባባይ ምሥጢር ነው።

መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ገድሎ በአፅማቸው ላይ ዙፋን ዘርግቶ አሥራ ሰባት ዓመት ሙሉ ፈንጭቶበታል። የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም አጐት ካሣ ከበደ ደግሞ ዛሬ በአፄ ዓምኃ ሥላሴ ቤት እንደ ልብ እየገባ መውጣቱ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደም መላሽ አለመኖሩን በንግሥቲቱ ምሥጢር አቀባይነት ገምቶ ነውና ቤቱ እውነት ባዶ ሆኗል ወይ?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደም፣ በመንግሥቱ ኃይለ ማርያምና በካሣ ከበደ ስለ ተጨፈጨፉት ወጣት ኢትዮጵያውያን፣ ስለ ሚኒስትሮቹና መኳንንቶቹ ዕልቂት ሁሉ ፍርዱን ለናንተው ትተናል።

ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ቢወልደኝ ንጉሥ፣ ብወልደው ንጉሥ ብለው በወጨረሻይቱ ሰዓት የጊቢ ሚኒስትር ሆነው ከተሾሙ በኋላ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሱትን በደል በቅደም ተከተል ከዚህ በላይ ዘርዝረነዋል።

የመንግሥቱ ኃይለ ማርያምን የትውልድ ዘርፍና ታሪክ በሙሉ በሚቀጥለው ጋዜጣችን እንዘረዝራለን።

ይቀጥላል......

የአንድነት ጥሪ

ክርስቲያኑ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም፣
እስላሙ ወገናችን በነብይ አላህ መሐመድና በአላህ ስም፣

ጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ክርስቲያኑም ሆነ እስላሙ፣ ስለ ኅብረትህና አንድነትህ እንድትሰባሰብ ይህ ጽሑፍ የእናት አገርህ ጥሪ መሆኑን ዕወቅ። በብሔርና በጐሣ፣ በፓርቲና በሃይማኖት ተለያይተህ እንድትበታተን ታልሞብሃል። ኢትዮጵያዊነትህ እንዲበጣጠስና ነባር ታሪክህ እንዲጠፋ ተሞክሯል።

ኤርትራዊውንና ትግሬውን ወገንህን ፍፁም እንድትጠላውና የባህል፣ የፊደል፣ የቋንቋ ግንኙነትህን እንድታፋልስ ተጥሮብሃል። ኤርትራዊውም ሆነ፣ ትግሬው ሁሉ፣ የራስህ ወገኖች ስለ ሆኑ፣ አንድነትህን አጥብቀህ በደምህ ገንባው "ሞዓ አንበሳ፣ መድህን፣ የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት አባሎች እንዲሁም ይድሐቅ" በማለት የተሣሠረውንና ታሪከኛው የከፋኝ አርበኛ ሁሉ፣ ለዚህ ደካማ የወያኔ ፖለቲካ ትበገራለህ ብሎ የሚያምን ኢትዮጵያዊ ይኖራል ማለታችን ሳይሆን፣ አንድነትህን በመፈታተን ላይ መሆናቸውን ለመግለፅ ነው። ኢትዮጵያዊው ወገንህ እየታሠረና እየተረሸነም መሥዋዕትነቱን ላንተ አስረክቦ በማለፍ ላይ ይገኛል።

የዚህን ዓይነት ጀግና ሕዝብ ታሪክ ተረክበህ ለተተኪው የምታስተላልፍ ራስህ እንጂ፣ ሌላ ተተኪ አይኖርም። ይኸም ራሱ ለእናት አገርህ ቃል ኪዳን የገባህላት በዚህች አገር የተወለድህ ቀን መሆኑን ዕወቅ። ካንተ ከውድ ልጇ በስተቀር ሌላ መሥዋዕት የሚሆንላት የለም። እናት አገርህ በጠላቷ ዕጅ ወድቃና በደም ተበክላ አፈር ላይ ስትወድቅ እያየህ ልታልፍ የማትችል አንተን የመሰለ ወንድ ልጅ ወልዳለች። "እኔ አለሁልሽ በል!!"

"አገር የጋራ፣ ሃይማኖት የግል መሆኑን" ካረጋገጥህ ብዙ ዘመናት አልፈዋል። ጀግኖች ልጆቿ እስከ ዛሬ አሳፍረዋት እንደማያውቁ የአምስት ሺህ ዘመናት የነፃነቷ ታሪክ ምስክር ሆነው ጋብዘውሃል። አንተም የዚህ ዘመን ተተኪ ትውልድ የእናት አገርህን የአንድነት ጥሪ ተቀብለህ ተነሣ!! ይህ ጥሪ የክተት አዋጅ ነውና ሕይወትህ ቆሞ የእናት ኢትዮጵያን ሞት ለማየት እንደሚዘገንንህ በማመን፣ ጥሪውን ላንተው ለኢትዮጵያዊው አስርክበናልና ይበቃሃል! ተነሣ!! ተነሣ!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት

የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረቶች የምንላቸው በልዩ ልዩ ዓይነት የተመዘገቡና፣ ቋሚነታቸውም የታወቀ፣ የሚንቀሳቀሰውና የማይንቀሳቀሰው ንብረቶች ናቸው።

ለምሳሌ በጂቡቲ ወደብና በየመን ወደብ የሚገኙት መርከቦች የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች ተብለው ይጠራሉ። እነዚህም መርከቦች በአፄ ኃይለ ሥላሴ የተገዙና በስም ዝርዝራቸው የታወቁ ሆነው ይታያሉ።

በኢትዮጵያም ሆነ በጐረቤት አገር የሚገኙ የጦር አይሮፕላኖች ሁሉ፣ የሚንቀሳቀሱ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት አይሮፕላኖች ተብለው ይጠራሉ። ሌሎቹም የንግድ አይሮፕላኖች በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተገዝተው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጡ የተደረጉ ሲሆን፣ አይሸጡም አይለወጡም። ንብረትነታቸውም የኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ንብረት ተብለው ለዘለዓለም ይኖራሉ።

የደርግ ሊቀ መንበር የነበረው መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በብሔራዊ ባንክና በጠቅላይ ግምጃ ቤት የነበረውን "የሚዛን ተፈሪ" አዶላ ወርቅ ሰብስቦ ወደ ራሱ መኖሪያ ቤት አዙሮ ዘብ አቆመበት። አክራሪው የኢህአፓ ኮሚዩኒስት፣ በአሜሪካዊው የአፍሪቃ ክፍል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር "በኮሔን" ረዳትነት "ከአሲምባ" ገሥግሦ መነገለው። ይህ ከመደረጉ በፊት መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የአዶላውን ወርቅ በካሣ ከበደ አማካይነት "ስዊስ ባንክ" ማስቀመጡ ይታወሳል። ግማሹንም ወርቅና "ሐሺሽ" ለመነገድ ወደ ሕንድ አገር ልኮ፣ መልዕክተኛው ታማኝ የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ወገን ከነወርቁና ከነሐሺሹ ተይዞ በሕንድ ጋዜጣ ሁሉ ወጥቶ ነበር። መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ስዊስ ባንክ ወርቅ ሲያስቀምጥ፣ አጐቱን ካሣ ከበደን የስዊስ አምባሳደር አድርጐ ሾመው። ስዊስ አገር የነበረውን የኢትዮጵያ ኤምባሲ ለመግዛት፣ በየወሩ የሚከፈለው የቤት ኪራይ፣ በመጨረሻው የቤቱ ግዢ ሆኖ ገንዘቡ በዚህ ዓይነት እንደሚጠቃለል፣ በዚያን ጊዜ ካሣ ከበደ ሰጥቶት የነበረው ቃለ መጠይቅ ያስረዳል።

ሔሞና ናትሩ የተባሉ የኢትዮጵያ የጦር መርከቦች በጂቡቲ ወደብ ላይ ሲንሣፈፉ

በስዊስና በሌሎቹም አገሮች ተቀማጭ ሆነው የተመዘገቡ ጥሬ ገንዘቦችና ወርቆች የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሀብት ተብለው ይጠራሉ። የንጉሠ ነገሥቱም ሆነ የሌሎች ንጉሣውያን ቤተ ሰብ ሀብቶች ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወረሰውም ሀብት በሙሉ፣ በዚህ የሥቃይና የመከራ ወቅት ንጉሠ ነገሥቱ ተረክበው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ በጥረት ላይ ይገኛሉ። የኢትዮጵያም ሕዝብ አገሩን ከመከራና ከሥቃይ ለማዳን በረኃብ እያለቀ፣ ትግሉን ጭምር በሚያፋፍምበት በሁኑ ወቅት፣ የገንዘቡ አመዳደብ በኢኮኖሚ ሊቃውንት እየተጠና በመደንገግ ላይ ይገኛል። በዚህም አንገብጋቢ ወቅት ኢትዮጵያዊ ሁሉ በዘርና በፓርቲ ሳይገነጣጠል አንድነቱን አጥብቆ እናት አገሩን ከአክራሪው የወያኔ ኮሚዩኒስት መንጋጋ እንዲያላቅቃት ይጠየቃል።

ዝግጁታችን እርገጠኛ ነው።

ኢትዮጵያ በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም አማካይነት የሶቭየት ኅብረት ደንበኛ ባሪያ ሆና ቆየች። በዚሁ ምክንያት ለአሜሪካና ለሶቭየት ኅብረት "ኃያላን መንግሥታት" የጦር ሜዳ ሆና ኖረች። ዛሬም በዚሁ ምክንያት ዘመናዊ ዲሞክራሲ ላልተዋጠለት አክራሪ ኮሚዩኒስት ዕጅ ወድቃ ኢትዮጵያ ሥቃይዋን ታያለች። ይህ ብቻ ሳይሆን፣ አገራችን በረኃብ አለንጋ እየተገረፈች፣ ከዓለም ኅብረተ ሰብ ምግብ ለማኝ ሆና ትገኛለች። ሥቃይና ሞት የተፈራረቁባት ኢትዮጵያ የበለፀጉ ዓለማት እስካሁን ለችግሩዋ መፍትሔ አላገኙላትም። ዲሞክራሲና የነፃ ገበያ ኤኮኖሚ እንዳይመሠረት፣ ወያኔ አገሪቱን በብረት መጋረጃ ዘግቶታል። ዓለምን በማታለል ተወቃሹ እንዳይታወቅ ጋርዷታል። ሠላም ባገሪቱ ወስጥ እንዳይሠፍን አፍኗል። ደካማውን ማርክሲስት በመገልበጥ አክራሪውን ማርክሲስት የመሠረተው የአሜሪካን ሪፑብሊካን ፓርቲ ከወቀሳና ከቂም ሊተርፍ አይችልም።

ዩናይትድ ስቴትስ፣ ሶቭየት ኅብረትና የተባበሩት መንግሥታት ተወካዮች ሁሉ ቀደም ሲል

ወደ ገጽ 11 ይዞራል

ከገጽ 10 የቀጠለ

በኢትዮጵያ ውስጥ ነበሩ። ዛሬ ደግሞ ለረኃብተኛው በምግብ አቅራቢነት ገብተው ሲያጋፍሩ ይገኛሉ። ይኸው ረኃብ ከመድረሱ በፊት በጦር ሠራዊትነት፣ የጦር መሣሪያ ይዘው የገቡና፣ ሰላም ያመጡ መስለው ኢትዮጵያን ለዚህ ሁሉ መከራ የዳረጉ፣ የቀበሮ ባሕታዊ መሆናቸውን እናውቃለን።

ሥልጣን፣ ገንዘብና ራስ ወዳድነት፣ ወደ ጦርነት እንጂ ወደ ሠላም ይመሩናል ማለት ዘበት ነው። በኢትዮጲያም ውስጥ የሚዋደቀው የሞዓ አንበሳ አርበኛ ሁሉ፣ ሕዝቡ በዲሞክራሲ መብቱ በምርጫው ስላልተጠቀመ "ከዘልዓለም ባርነት የአንድ ቀን ነፃነት" መርጦ እየተዋጋ ነውና የገንዘብና የሞራል ድጋፍ ይጠበቅብናል። ከጐኑም ተሠልፈን ለመዋጋት ዝግጁነታችን እርግጠኛ ነው።

ታሪክን በደማቸው የገነቡ

እውነትም ታሪክ ነው፣ ትግሉ ተጀመረ
ታሪክ ያልገነባው፣ መሪ መች ነበረ።
በጐሣ ቢለያይ፣ በታሪክ አንድ ነው
ታሪክም አይሞትም፣ ጊዜም አይሰርዘው።
ነበሩን አባቶች፣ ታጣቂ መቀነት
በጠንካራ መንፈስ፣ ርሃብ የሚገቱበት።
ፈትል እጀ ጠባብ፣ ነበር ፈትል ሱሪ
ያገርን ነፃነት፣ ለትውልድ አብሳሪ።
ሕይወታቸው ረዥም፣ ኑሮአቸው ጠባብ
ታሪካቸው ቋሚ፣ እንደ ፋሲል ግንብ።
ያገርን ነፃነት፣ ለኛ ሲያስረክቡ
የአክሱምን ደወል፣ ነበር ያስተጋቡ።
ወሬ የሚያፍተለትል፣ አልፎ ከነፍጠኛ
አያውቁም ነበረ፣ ፍፁም ጋዜጠኛ።
ወሬኛ ይሉታል፣ ስሙን እየናቁ
በኑሮ ላይ ትግል፣ መኖሩን ሳያውቁ።
ይወረሳልና፣ በጽሑፍ የቆየ
በአፍ የሚነገር፣ ምን ላይ ቆሞ ታየ።
"አንድ ወሬኛ አገር ይፈታ
አንድ ቅማል ሱሪ ያስፈታ"
ይሉ ነበር አበው፣ ስለ ጋዜጠኛ
ይወደድ ነበረ፣ ወታደር ነፍጠኛ።
ታላቁ ቴዎድሮስ በአንደበታቸው
ከሺ ነፍጠኛ አንድ ወሬኛ ማለታቸው።
ማጋነናቸው ነው፣ ስለ ጋዜጠኛ
አሁን በነበሩ፣ ታላቁ ነፍጠኛ።
ቅኝ ገዢ ኢትዮጵያን፣ ለመያዝ ሲመጣ
አባ ታጠቅ ካሣ፣ መድፉን ይዞ ወጣ።
ካዲስ መሣሪያ ጋር እንዳይወዳደር
ቴዎድሮስ አቅቶት፣ ተቸግሮ ነበር።
በዚሁ ጊዜ ነው፣ ጀግናው አሽከራቸው
ገብርዬም የሞተው፣ ዋናው ታማኛቸው።
እንግሊዞችም ያኔ፣ ሕይወትን ሳይነኩ
ተሩውሩጠው ነበር፣ ካሣን ሊማርኩ።
ጀግናው ግን ሽጉጡን፣ ግንባር ላይ ተክለው
ጥይቷን ጠጥተው፣ ለመሞት ቆርጠው።
ገብርዬ ከሞተ፣ ሕዝባችን ካለቀ
ወንድ እጁን አይሰጥም፣ አለቀ ደቀቀ!
ሲሉ ለኛ ክብር፣ ጀግናው ቴዎድሮስ
የተሠው ናቸው፣ የታሪክ ንጉሥ።
መላ ቅጡ ጠፍቶ፣ አገር ተዝረክርኮ
ማሠሪያው ሲጠፋ፣ ቡከን ተፍረክርኮ።
ተነሥ ያገሬ ልጅ፣ ትጥቅህን አጥብቀው
ለታሪክ መሥዋዕት፣ መሆንክን እወቀው።
የኋላ ዙር የለም፣ ተንዝ ወደ ፊት
እጠፍ ተራራውን ያንን ቁልቁለት።
ራስህ ሥራበት፣ ታንኩን ቀምተህ
በቦምብ አፈራርሰው ኑሮህን ትተህ።
ውስጥ አንጀቴ ደብኖ፣ አረረ ከሰለ
ኢትዮጵያዊ መልኬ፣ ጥቀርሻ መሰለ።
አሮ ውስጥ አንጀቴ፣ ሐሞቴ ፈሰሰ
ያ ያበሻ መልኬ፣ ከሰል ቅብ ለበሰ።
ባድዋ ድል ጦርነት አቂመው ሲኖሩ
ፋሽስቶች በመርዝ ጪስ፣ ኢትዮጵያን ወረሩ።
ከኛ ጋር በመሆን፣ ግንባር ተሠልፈው
ፋሺስትን በማይጨው ተጋድለው ጨፍጭፈው።
ያሜሪካን ጭቁሮች፣ ታሪክ መሠረቱ
በኢትዮጵያ ላይ፣ ቋሚ ችካል መቱ።
ጥቁሩ አሜሪካዊ፣ የሚያውቅ ያገር ልክ
የሣባ ወንድ ልጆች፣ ሲል ጽፏል ታሪክ።
ታሪኩን ዘርዝሮ፣ በጻፈው ገጾች
አጋኖ ታል ግሩም፣ የሣባን ልጆች።
በመከራ ጊዜ፣ ደሙን አፍሶላት
የነበረ ሲሆን፣ የኛ አገር የሱም ናት።
ጥሪይድረሳቸው፣ አሁን በጠቅላላው
የናንተው አገር ናት፣ ኢትዮጵያ በሞላው።
ያሜሪካን ጥቁሮች፣ ከቶ የማይረሡ
ትንሣኤ ነውና፣ እነሱም ይነሡ።

በኮንግሬስ የተካሔዱ ውይይቶች

እንደ አውሮጳ ዘመን አቆጣጠር ሐምሌ 27 ቀን 1994 በዩናይትድ ስቴትስ ታላቁ ምክር ቤት ስለ ኢትዮጵያ ጉዳይ ልዩ የሆነ ከፍተኛ ውይይት ተካሔዷል።

የዚህም ከፍተኛ ውይይት ተካፋዮች ሆነው በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ተጋብዘው የነበሩት ባለሥልጣኖች በአሜሪካን መንግሥት ቁልፍ የሆኑ ሥፍራዎችን ይዘው እንደሚያሽከረክሩ ታውቋል። እነዚህም ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ብዙ ገፅ ያዘሉ ማስረጃዎችን ለኮንግሬሱ በማቅረብ ጉዳዩን በጠቅላላው ለመግለፅ ችለዋል። ማስረጃዎቹን በዝርዝር ቀርፀው ያቀረቡትም ባለሥልጣኖች የሚከተሉት ናቸው።

Associated Press

Herman Cohen

የአሜሪካን መንግሥት ረዳት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር "ምስተር ጂዮርጅ ኢ ሙዝ፣" የአሜሪካን መንግሥት የአፍሪቃ ጉዳይ ረዳት የአስተዳደር ኃላፊ፣ "ምስተር ጆን ኤፍ ሒክስ፣" የቀድሞው የአፍሪቃ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረው "ሔርማን ኮሔን" የኢትዮጵያ የአይሑድ ሃይማኖት ተከታዮች ፈላሾችን ለዕሥራኤላውያን እንዲሸጡ አስደርጐ ለመንግሥቱ ኃይለ ማርያም አምሳ ሚሊዮን ዶላር በመስጠት የባሪያ ሽያጭ ያካሔደውና ንፁሕ ኢትዮጵያውያንን በገንዘብ ያሸጠ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት በመጨረሻውምደሞ ከኤርትራ የማኦ ሴቱንግ አክራሪ ኮሚዩኒስት ርዕዮተ ዓለም የተጠመቀውን ኢሣይያስ አፈውርቂንና ሌላውንም የኢህአፓ አክራሪ ኮሚዩኒስት መለስ ዜናዊን ተመሳጥሮና መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ሲያስገለብጥ የኢትዮጵያን የወደፊት ዕድል ሳይገመግም፣ በአንድነት ተሣሥራ ለአምስት ሺህ ዘመናት የኖረችውን ነፃ አገር፣ ዛሬ የወያኔ መጫወቻ ሆና በዘርና በጐሣ ተለያይታ የደም ጐርፍ እንዲወርድባት ያስደረገ ጠላታችን "ሔርማን ኮሔን" ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በመካሔድ ላይ ስለሚገኘው የሰብዓዊ መብት አሠቃቂና አደገኛ አዝማሚያ የምስክርነት ቃላቸውን በማስረጃ እያስደገፉ ያቀረቡት "ምስተር አብዱላሂ ናኢም" ናቸው። .

ከኦክላሆማ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ፖለቲካል ሣይንስ ክፍል ስለ ኢትዮጵያ ውድቀት በዝርዝር ያስረዱት "ምስተር ቴዎዶር ኤም ቬስታል " መሆናቸው ታውቋል።

እያንዳንዳቸው ባቀረቡት በቂ ማስረጃ ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ የምትገኝበትን ውድቀትና የሚያስከትለውንም አደጋ ሊደብቁት አልቻሉም። እያንዳንዱ ባለሥልጣን ለዚህ ታላቅ ምክር ቤት ያቀረበውን መግለጫ በየስሙ ተርጉመን እስክናቀርበው ድረስ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን አንባቢ እንዲመለከተው አድርገናል።

ከደርግና ከወያኔ ጋር የተደረጉ ጦርነቶች

ከሐምሌው እትም የቀጠለ......

በብሔራዊ ጦር የሚመራው ሕዝባዊ ሰራዊት ከደርግና ከሻቢያ እንዲሁም ከኢሕአፓ ጋር በተደረገው ጦርነት መሥዋዕት ሆኗል። በአገር ውስጥና በውጭ አገር ፀረ ዘውድ ፀረ ኢትዮጵያ ከሆኑት ጠላቶች ጋር ከፍተኛ ትግል አከሔዷል። አሁንም በሞዓ አንበሳ ስም ከየአቅጣጫው እየተዋጋና እየታገለ ይገኛል። በወያኔና በሻቢያ ብዙ ሰላማዊ ሰዎች በሞዓ አንበሳ ስም እየታፈኑ ተወስደው ተገለዋል። በመታሰርም ግፍ ተፈፅሞባቸዋል። ታሰሩ የተባሉትም የሞዓ አንበሳ ደጋፊዎች እስካሁን የት እንደደረሱ አይታወቅም ያልታደለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ንጉሠ ነገሥቱ ሊመለሱልን ነው ተብሎ ሲነገረው ዳር እስከዳር ግልብጥ ብሎ መጣ፣ የሞዓ አንበሳ ደጋፊ ሆኖ በሃይማኖት መሪዎች ይበጅሃል ተብሎ ተሰበከ፣ የሞዓ አንበሳ ጽ/ቤት በሚገኝበት ሁሉ ተመዝግቦ ሁሉም በያለበት ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ አገራቸው መመለስ በዝግጅት ይጠባበቅ ነበር። የንጉሠ ነገሥቱን ጉዞ የተሰረዘበትን ምክንያት ባለፈው እትማችን ገልጸናል። ለወደፊትም በዝርዝር ይገለጻል።

በሞዓ አንበሳ ስም ንጉሠ ነገሥቱ ይመጣሉ ተብሎ ለጠላት የተጋለጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የሞዓ አንበሳ ደጋፊ ነህ በመባል በመንግሥት እጅ በሚገኝበት ማከፋፈያ ድርጅቶች ከሚሰጠው ስኳርና ዘይት የምግብ እርዳታ ተከልክሎ በረሐብ አለንጋ የሚሰቃየው ወገናችን ከጊዜ ወደጊዜ እየባሰ ሄዷል።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ አምኃ ሥላሴ የሞዓ አንበሳን እንደገና መቋቋም በካፒታል ሒልተን ሲመርቁ፣ ጄኔራል ዓባይ የማኑ የልዩ ጽ/ቤቱም ሹምና የበላይ ዋና ተጠሪ በጐን ተቀምጠው ይታያሉ።

በየጠቅላይ ግዛቱ አውራጃና ወረዳዎች ተከፍቶ የነበረው መሥሪያ ቤት ተዘግቷል። የሞዓ አንበሳ አባላት በሚደርስባቸው በደል አቤቱታ የሚያሰሙበት ዳኛ አጥተው በመንገላታት ላይ ይገኛሉ።

በሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ በሞዓ አንበሳ ጽ/ቤት የሚውለበለበውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የወያኔ ታጣቂዎች ከተሰቀለው እያወረዱ በእሳት እያቃጠሉና ኃላፊዎችን በመግደል ባደረሱት ግፍ የሞዓ አንበሳ ደጋፊዎች በከፈቱት ጦርነት ብዙ የወያኔ ተዋጊዎች ተገለዋል። በአሁኑ የሞዓ አንበሳ ተዋጊዎች በወያኔ ታጣቂዎች ግፍ ተነሳስቶ በመዋጋት ላይ ይገኛሉ።

ይቀጥላል......

ኰሎኔል ሣሙኤል ይቅርታ ጠየቀ?

ስሙ ኰሎኔል ሣሙኤል ይባላል። ቀድሞ የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን አሽከር ነበር። የኰሎኔል ሣሙኤል ልጅ ነቢዩ ሣሙኤል የተባለው የወያኔዎች አሽከር ሆኖ ጭራውን በመቁላት ላይ ይገኛል።

ኰሎኔል ሣሙኤል በቅርብ ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አምኃ ሥላሴን ለመጐብኘት ወደ አሜሪካን አገር መጥቶ ነበር። የመጣውም ንጉሠ ነገሥቱን ለመጐብኘት ሳይሆን፣ ሁኔታውን ለመሰለል በወያኔዎች ተልኮ ነው። ይኸንኑ የኰሎኔል ሣሙኤልን አመጣጥና ለስለላ መሆኑን ለንግሥቲቱ ቢነገርም ሳይቀበሉ ቀርተው አስገቡት። ጥንትም ቢሆን ታማኝነቱ ለንግሥቲቱ እንደ ሆነ የማያውቅ የለም።

ኰሎኔል ሣሙኤል በአሜሪካን አገር ከተመለሰ በኋላ፣ በንግሥቲቱ በኩል ምሥጢሩን ሁሉ ለወያኔ ገልጾ፣ የሞዓ አንበሳ ተወካይ ነኝ ማለቱንና እንዲያውም ወያኔን እንድደግፍ ንጉሡ አዘውኛል ብሏል። ሞዓ አንበሳ የዘውድ ምክር ቤት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች የሚመሩትና ልዩ ጽ/ቤት ከአስባሳቢ አካል ጋር መሥርቶ የሚያስተዳድር መሆኑን ኰሎኔል ሣሙኤል አላወቀም።

እቴጌይቱ የፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን ያላቸው መስሎት ከትምህርቱ ጉድለት ጋር የተሸከመው የድንቁርና ሸክም ጀርባውን አጉብጦታል።

ከዚህ ሁሉ ድንቁርናው ጋር ኤርትራ ድረስ ሔዶ ኢሣይያስ አፈወርቂና የቻይናው ኰሚዩኒስት ተከታዮቹ፣ ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ ላደረሰችው ጦርነትና ደም መፋሰስ ኤርትራ ለኢትዮጵያ ይቅርታ እንድታደርግ ጠይቋል። ለዚህ ዓይነት ጉደኛ ከርሳም የኢትዮጵያ ሕዝብ በቅርብ ቀን መልሱን እንደሚሰጠው እርግጠኞች ነን።

ይቀጥላል።

የታሪክ እንቅፋት

ከሐምሌው እትም የቀጠለ

መጋቢት 27 ቀን 1985 የዘውድ ምክር ቤቱ ለግርማዊት እቴጌ ሙድፈሪያሽ ወርቅ ያስተላለፈው ውሳኔ እንደሚከተለው ነበር።

የግርማዊ ቀዳማዊ አምኃ ሥላሴ የዘውድ ምክር ቤት

CROWN COUNCIL

ለግርማዊት እቴጌ መድፈሪያሽ ወርቅ
የቀረበ ምክር ቤቱ ያስተላለፈው ውሳኔ

መጋቢት 27 ቀን 1985 ዓ/ም

ግርማዊ ጃንሆይ ከታሪክ የወረሱትንና የኢትዮጵያም ሕዝብ የጣለባቸውን አደራና ኃላፊነት ለመወጣት ሲሉ በተለሙት መሠረት የሞዓ አንበሳ ዙፋናዊ አስባሳቢ አካል እስካሁን ሕዝቡን በማደራጀት የፈጸመው ተግባር ሁሉ ከፍተኛ ውጤት ማስገኘቱን በመመልከት ወደፊትም እንደዚሁ ሥራው እንዲቀጥል ደጋግመው የሰጡት መሪ ቃል ይታወሳል። ከእንግዲህ ወዲያ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ ማለት ተገቢ አለመሆኑን በማስረዳት የተደከመበት ሥራ ሁሉ መና ሆኖ እንዳይቀር በታሪክም ተወቃሽነትን እንዳያስከትል ሥራው በተሟላ ሁናቴ እንዲካሄድ ፈቅደው አስፈላጊው በጀት እንዲከፈል ደጋግመው ግርማዊነታቸው በሰጡት መሪ ቃል ገንዘብ አለን ወጭ ሆኖ እየተከፈለ ሥራው ይቀጥል በማለት ለግርማዊት እቴጌ ትዕዛዝ ሲሰጡ የምክር ቤቱ አባላት ተገኝተን ሰምተናል። ይህ ንጉሣዊ ውሳኔና ትዕዛዝ በግርማዊት በኩል እስካሁን ተገቢው ክብደት ተሰጥቶት በተግባር ላይ ባለመዋሉ ሥራው ተበድሏል፣ የንጉሠ ነገሥቱም ክብር ተነክቷል።

ምክር ቤቱ በንጉሠ ነገሥቱ የተጣለበትን አደራ በታሪክም ያለበትን ተጠያቂነት ለመወጣት በጉዳዩ በሰፊው ከተወያየበት በኋላ ከሚከተሉት ውሳኔዎች ላይ መድረስ ግድ ሆኖበታል።

1. የንጉሠ ነገሥቱን ክብር በሚመለከት
=====================

በሕገ መንግሥቱ እንደተደነገገው ንጉሠ ነገሥቱ ክብሩ የማይደፈር ቃሉ የማይገሠሥ ትዕዛዙ የማይጣስ መሆኑ እየታወቀ ውሳኔያቸውና ትዕዛዛቸው አለመከበሩና አለመፈጸሙ ምክር ቤቱን ከማሳዘኑም በላይ በቀላሉ የማይታለፍ በሕዝብና በታሪክ ዘንድ የሚያስጠይቅ ሆኖ አግኝቶታል።

2. ሥራውን በሚመለከት፣
============

ሕዝቡ በተገባለት ንጉሣዊ ቃልና በተደረገውም ከፍተኛ ቅስቀሳ ለዘውዱ መመለስና ለአገሩም አንድነት መጠበቅ ብዙ መስዋዕትነት እየከፈለ ሳለ ሥራው በበለጠ አስተማማኝነት እንዲቀጥል በማድረግ ፋንታ በአሁኑ ወቅት ባጀት መከልከሉ በሮ እንዲዘጋና ሥራው እንዲዳፈን አድርጎታል።

በዚህ ጉዳይ ግርማዊት እቴጌ መልስ ሲሰጡ የነበረንን ዘጠኝ መቶ ሺህ ዶላር አምጥቼ ለሥራውና ለቤት ጉዳይ ውሏል። በዚሁም ወጭ ዝርዝር በሂሳብ እንዲጣራ ፈቃደኛ ነኝ ብለዋል። ጃንሆይም ያላቸው ይህ ብቻ አለመሆኑን በመግለጥ ግርማዊት የሰጡትን መልስ አልተቀበሉትም። ስለዚህም በጠቅላላ በኦዲት ተጣርቶ እንዲቀርብ ንጉሣዊ ትዕዛዝ ሰጥተዋል።

ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት በግርማዊነታቸው በኩል ገንዘብ አለን ሥራው ይቀጥል እያሉ በግርማዊት በኩል ደግሞ ገንዘብ የለንም የሚሉትን ምክር ቤቱ ለመቀበል አዳጋች ሆኖ አግኝቶታል ስለዚህ ሥራው እንዳይበደል የግርማዊ ጃንሆይ ትዕዛዝ በተግባር ላይ እንዲውል በታላቅ ትህትና እናስገነዝባለን።

ወ/ሮ ዘነበ ወርቅ አራጋው
አፈ ንጉሥ ተሾመ ኃ/ማርያም

ጄኔራል ዓባይ የማኑ
ዶ/ር ጌታቸው መካሻ